በስመ እግዚአብሔር አብ፥ ወወልድ፥ ወመንፈስ፡ ቅዱስ፡ አሐዱ አምላክ፤
በስማ ለእምነ ወለንግሥትነ ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ፤
በኃይለ መስቀሉ፡ ለመድኃኒነ፥ ወለካህንነ፥ ወለንጉሥነ ኢየሱስ ክርስቶስ፡፡

# "ጾመ ኢትዮጵያ"

## ይህ፡ ኢትዮጵያዊው ትውልድ፡

በ፳፻ (በ፪ሺ) ዓመተ ምሕረት፡ ለጥቂት ጊዜ የተፈታው ዲያብሎስ፡
በተለይ፡ በዚህ፡ በ፳፻፯ተኛው (፪ሺሰባተኛው) ዓመተ ምሕረት፡
የሚያስከትልበትን የፈተናና የችግር ማዕበል፡
በድል አድራጊው አንበሳ፡ በኢትዮጵያዊው ኢየሱስ ክርስቶስ
እና እጆቿን፡ ወደእርሱ በዘረጋችው፡
በኢትዮጵያዋ ቅድስት እናቱ ድንግል ማርያም የቃል ኪዳን ኃይል፡
እስከዛሬ፡ በየዓመቱ፡ ሲያካኺድ በቆየው፡
በዚህ፡ በጾመ ኢትዮጵያ ምሕላው አማካይነት፡
ዘንድሮም ተቋቁሞ ለማስወገድ ስለሚችልበት መፍትሔ
የሚያመለክተውን መልእክት፡
ዛሬም እንደገና፡ የሚሰማ ጆሮ ያለው፡ ይስማ!

## ይድረስ፡-

**በኢትዮጵያ ላላችሁትና በመላው ዓለም ለተበተናችሁት፥**
**በተለያየ የኑሮ ኹኔታና የሥራ መስክ ለምትገኙ፥**
**በልዩ ልዩ ተግባርና ሙያም ለምታገለግሉ፥**
**በአጠቃላይ፡ እንደኢትዮጵያ ሥርዓተ መንግሥት፡**
**የቤተ ሕዝቡ፥ የቤተ ክህነቱና የቤተ ምልክናው አባሎች ለኾናችሁት፡**
**ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት!**
**ለወንዶቹም፥ ለሴቶቹም! ለአዛውንቱም፥ ለወጣቱም!**
**በየግላችሁም! ለኹላችሁም!**

---

"እንደምን ከርማችኋል!? ባጅታችኋልም!?" እያልን፡ በልዑል እግዚአብሔርና በቅድስት እናቱ ድንግል ማርያም ስም፡ ኢትዮጵያዊ ሰላምታችንን፡ እናቀርብላችኋለን።

ለቅዱሱ ኪዳን ዓመታዊ ሕይወታችን ብሶል (compass) ኾኖ ይመራን ዘንድ፡ "ኪዳናችን!" በተባለው፡ መጽሔታችን አማካይነት፡ በየዓመቱ የሚወጣው የዘመን መቍጠሪያችን፡ በእያንዳንዱ የዓመቱ ወር የሚውለውን፡ የአጽዋማትና የበዓላት፥ የተዝካረ ቅዱሳንና የዕለታት ቅዱሳት መደበኛ መታሰቢያና መከበሪያ የኾነውን ቀን ለይቶ የሚያሳየንና የሚያስታውሰን ሠንጠረዥ መኾኑን፡ ኹላችሁም፡ ስለምትገለገሉበትና ስለምትጠቀሙበት ታውቁታላችሁ።

በጽሕፈት ጠረጴዛችሁ ላይ በተዘረጋው፥ ወይም በግድግዳ ላይ በተንጠለጠለው፡ በዚህ፡ በ፳፻፯ (፪ሺ፯) ዓመተ ምሕረት የቀን መቍጠሪያችን ሰሌዳ ውስጥ ያለውን፥ በተለይ፡ ይህ፡ የጾመ ኢትዮጵያ ምሕላችን የሚውልበትን፡ የዘንድሮውን፡ የጥርንና ተከታዩን የየካቲትን ወራት ስንክሣር ገልጣችሁና አተኵራችሁ ስትመለከቱ፡ ምንን ታያላችሁ? ታላላቅ ድርጊቶች የተፈጸሙባቸውንና የትንግርት ኹኔታዎች የተገለጹባቸውን፡ ገናና ዝክረ ነገሮቻችንን ይዘው ታገኟቸዋላችሁ።

ከእነዚህ መካከል፡ ዋና ዋናዎቹን ለመጥቀስ ያህል፡ ከዚህ እንደሚከተለው፡ በየመልካቸው ተዘርዝረው ቀርበዋል። እነርሱም፡ አጠቃላዩን የአገራችንን ዜና መዋዕል በሚመለከት፡ በተለያዩ ዘመናት፡ በቤተ ሕዝቡ፥ በቤተ ምልክናውና በቤተ ክህነቱ ላይ የደረሱት፡ ተመሳሳይና ተነጻጻሪ፡ የመከራና የድል ጽዋዎች የታዩባቸው ናቸው።

የሰሌዳው ሠንጠረዥ፡ በአንድ በኩል፡ የካቲት ፫ ቀን፥ ፲፭፻፴፪ ዓ. ም. የግሼን ማርያም አምባ፡ በአሕመድ ግራኝ ወራሪ ጦር የተመዘበረበት፥ ቀጥሎም፡ የካቲት ፲፰ ቀን፥ ፲፱፻፳፱ ዓ. ም.፡ የዚህኑ፡ የአሕመድ ግራኝን ወራሪ ጦር ሲከላከል በጀግንነት የተሠዋው፡ ኢትዮጵያዊው አዝማች ደገልሓን፡ በሰማዕትነት ያረፈበት፥ በመጨረሻም፡ የካቲት ፳፯ ቀን፥ ፲፭፻፴፭ ዓ. ም. ራሱ አሕመድ ግራኝ፡ ድል የኾነበት ቀን መኾኑን ይነግረናል።

በሌላ በኩል ደግሞ፡ የካቲት ፬ ቀን፥ ፲፱፻፲ ዓ. ም. "ብርሃን ዘኢትዮጵያ" የተባሉት፡ ስመ-ጥሩዋ የአድዋው ጦርነት ተባባሪ አዝማችና ባለድል፡ እቴጌ ጣይቱ ብጡል ያረፉበት ሲኾን፥ የካቲት ፳፫ ቀን ፲፰፻፹፰ ዓመተ ምሕረትም፡ ከዘመኑ የዓለም ልዑላነ ኃያላን፡ አንዱ የኾነው፡ የጣልያን ወራሪ ጦር፡ በዳግማዊ አጼ ምኒልክ መሪነት በዘመተው ሠራዊቷ ስለተደመሰሰ፡ "ኢትዮጵያ፡ ኃይሏ፡ በቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖቷ መኾኑ የተረጋገጠበት፡ የአድዋ ድል" ታስቦ ይከበርበታል።

ከዚህ ጋር፡ ይኸው የዘር ጠላት፡ በአኹኑ ጊዜ እየተደረገ እንደሚታየው ዓይነት፡ በዚያን ዘመንም፡ በኢትዮጵያ ላይ እንዲፈጽም የታዘዘበትን የቅጣት ግዳጅ ሊያከናውን፡ ጊዜውን ቆጥሮ፡ በ፲፱፻፳፰ ዓ. ም. የፋሺስትነት ስሙን አንግቦ፡ ለኹለተኛ ጊዜ፡ ተመልሶ መጥቶ እንደነበረ ይታወሳል፤ በአገሪቱ ላይ ተንሠራፍቶ ሊቆይ ቢሞክርም፡ በዚያው በገባበት ዓመት በተሠየፉት፡ ኢትዮጵያዊዉን ሰማዕት፡ ቅዱስ ጴጥሮስን በመሰሉት ታማኞች የኢትዮጵያ ልጆች መሥዋዕትነት፡ ባጭር ጊዜ ውስጥ፡ ተዋርዶና ተባርሮ፡ ከኢትዮጵያ ወጥቷል፤ ይኹን እንጂ፡ ከመውጣቱ በፊት፡ በአገሪቱ ላይ ባሰፈነው የጭካኔ አገዛዙ፡ ያፈሰሰው የንጹሓን ደም፡ "በ፲፱፻፳፱ ዓ. ም. በፋሺስት ጣልያን፡ የሰላማውያን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት የግፍ እልቂት፡ በአዲስ አበባ" ተብሎ በሚታወስበት፡ በየካቲት ፲፪ ቀን ተመዝግቧል።

ከይሁዲቷ ጉዲት አገዛዝ በኋላ፡ በ፱፻፴፫ ዓ. ም. "ዘአጉየየ" = "የአባረረ" በተባለው፡ በዛጔው አጼ መርሓ ተክለ ሃይማኖት አማካይነት፡ ኢትዮጵያዊው፡ የመልከ ጼዴቅ ሥርዓተ መንግሥት የተመለሰበት በዓል ታስቦ የሚከበረው፡ በዚሁ፡ በየካቲት ወር በሚውለው፡ በ፳፩ኛው፡ የኢትዮጵያዊቷ የድንግል ማርያም ቀን ነው።

ከኹሉም ይልቅ፡ ጎልቶ የሚታሰበውና ለእነዚህ ኹሉ፡ ድሎች ዋስትና፥ እንዲሁም፡ ለሰባቱ ቅዱሳት ኪዳናት ርእስና ማኅተም፥ ከዚህ የተነሣም፡ የቅዱሱ ኪዳናችን ዘውድ የኾነው፥ እርሱም፡ በድንግል ማርያምና በኢየሱስ ክርስቶስ የተገኘው፡ የኪዳነ ምሕረት ዓመታዊ ክብረ-በዓላችን የሚዘከረው፡ በዚሁ፡ በየካቲት ፲፮ ቀን መኾኑ ታውጆበት ይገኛል።

ይህ መደበኛ ኹኔታ፡ በዚህ ሥርዓት ተመሥርቶ እየተሠራበት እያለ፡ ቀድሞ፡ "ጾመ ነነዌ" ዛሬ ግን፡ "ጾመ ኢትዮጵያ" የምንላት፡ የሦስት ቀናቷ የምሕላ ትጋሃችን፡ ዘንድሮ፡ ከዚሁ፡ ከየካቲት ወር በሚቀድመው፡ በጥር ወር ማብቂያ ሳምንት ውስጥ ተካትታ እናገኛታለን። ይህችው ጾም፡ ከጥር ፳፭ እስከ ፳፯ ቀን፥ ፳፻፯ ዓ. ም. ድረስ እንደምትውል፡ ሠንጠረዡ ያረጋግጣል።

## ለአንክሮ ለተዘክሮ ያህል።

ከ፲፱፻፷፮ ዓ. ም. ጀምሮ፡ እስከዚሁ ዓመት ድረስ፡ ለአርባ ዓመታት ያህል፡ በተለይ፡ በየካቲትና በጳጉሜ ወራት፡ "ጾመ ኢትዮጵያ" እና "ሰላም ለኢትዮጵያ" በሚሉ ስያሜዎች፡ በየመንፈቀ ዓመቱ፡ ሲቀርብ የኖረው፡ የቅዱሱ ኪዳን የምሕላ ጾምና ጸሎት፡ "ኢትዮጵያዊ ነኝ!" የሚለውን ትውልዱን፡ በታላቁ ኃጢአቱ ምክንያት ከመጥፋት ለማዳን፡ አስተዋጽኦውን አበርክቷል፤ ከዚህም በላይ፡ ራሷ ኢትዮጵያን፡ ከቤተ ሕዝቧ፥ ከቤተ ምልክናዋና ከቤተ ክህነቷ ጋር፡ በዘለዓለማዊው የነጻነት ህልናዋ እንዳለች ኾና እንድትቀጥል በማድረጉ ረገድ፡ የድርሻውን ግዳጅ ፈጽሟል።

እንዳለፉት ተከታታይ ዓመታት ኹሉ፡ በዘንድሮዋም ጾመ ኢትዮጵያ፡ ይህ ትውልዱ፡ በየግሉም ኾነ፥ በቤተ-ሕዝቡ፥ በቤተ ክህነቱና በቤተ ምልክናው አማካይነት፡ እየራሱን፡ ለእውነተኛ ንስሓ አብቅቶ ቢገኝ እኮ፡ እያማረረው ካለው መከራና ሥቃይ፡ በድል አድራጊነት ወጥቶ፡ ኹለንተናዊዉን የትድግና አክሊል ሊቀዳጅ እንደሚችል፡ ምንም ጥርጥር የለውም። ያ፡ በነቢዩ ዮናስ አንዲት የስብከት ቃል፡ ወዲያው፡ ወደፍጹም ንስሓ የተመለሰው፡ የነነዌ ሕዝብ፡ በሦስት ቀኖች የጾምና የጸሎት ምሕላው፡ ከታዘዘ መቅሠፍት እንደዳነ ማለት ነው።

የነነዌ ነገር ከተነሣ ዘንድ፡ ከጥቂት ዓመታት በፊት፡ ልክ፡ የዚህችው የጾመ ኢትዮጵያ ምሕላ በሚጀመርባት የሰኞ አጥቢያ ሌሊት፡ የጥንቷ ነነዌ፥ የዛሬዋ ሊባኖስ መናገሻ ከተማ በኾነችው፡ በቤይሩት፡ የወረደውን መዓት፡ እዚህ ላይ፡ አኹንም፡ እንደገና ማዘከሩ አግባብ ይኾናል፤ እርሱም፡ ከዚያች ከተማ፡ ወደአዲስ አበባ ሊበር የተነሣው የኢትዮጵያ አየር መንገድ ጥያራ፡ ተከስክሶ በባሕር ውስጥ በመውደቁ፡ በኢትዮጵያና በሊባኖስ አገሮች ውስጥ የታየውን ኹኔታና የተፈጸመውን ድርጊት የሚመለከተው ጉዳይ ነው።

አዎን! ያ የመለኮት የማስጠንቀቂያ መልእክት፡ ለኹለቱም አገሮች ሕዝቦችና መንግሥታት በተላለፈበት፡ በዚያ አስደንጋጭና አሠቃቂ አደጋ ያለቁትን፡ ዜጎቻቸውን ሞት ምክንያት በማድረግ፡ በኹለቱም አገሮች ውስጥ፡ ለሦስት ቀናት፡ ሰንደቅ ዓላማዎች፡ ዝቅ ብለው እንዲውለበለቡና ሙታኑ፡ በብሔራዊ የኃዘን ውሎ እንዲታሰቡ፡ በመንግሥታቱ አዋጅ መታዘዙ፡ ሊወሳ ይገባል።

በዚህ መሠረት፡ ጥንታዊቷ የነነዌ ሕዝብ ይኖርባት የነበረችው፡ የዛሬዩቱ ሊባኖስና ጥንታዊቷን ጾም ወርሶ፡ ነገር ግን፡ ቅዱሱን ኪዳን ያፈረሰው የዛሬው የኢትዮጵያ ትውልድ፡ ኹለቱም፡ "ጾመ ኢትዮጵያን" በመራራ ኀዘንና ልቅሶ እንዲያሳልፏት ተደረገ። ስለዚሁ፡ የመርዶ ዘገባና ስለመለኮታዊ መልእክትነቱ፡ በጊዜው፡ በጎዋ ሰሌዳችን ላይ ሠፍሮ የነበረውን መግለጫ፡ ወደታች ታገኙታላችሁ።

እንግዴህ፡ እውነተኞቹ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ ምንጊዜም አጥተውት የማያውቁትን የምሕረት ጸጋ፡ ይኸው የዛሬው፡ ያልታደለው ኢትዮጵያዊ ትውልድ፥ መላውም የሰው ዘር ጭምር፥ በጠቅላላም፡ ኹሉም ፍጥረተ-ዓለም፡ ያገኙት ዘንድ ለማስቻል፡ በዚህም ዓመት፡ የተለመደ ምሕላችንን እናካኼዳለን።

ይህንም ስናደርግ፡ ሳናውቀው የቀረ ኖሮ አይደለም። በተለይ፡ ኢትዮጵያዊው ትውልድ፥ ባጠቃላይም፡ መላው ሰብአዊው ትውልድ፡ የእግዚአብሔርን ሥርዓት ለማፍረስ በመሞከርና በመጣር፡ ለምድራዊው ገንዘብ፥ ለሥጋዊው ጥበብና ለዓለማዊው የጦር ኃይል፡ በጣዖት መልክ፡ የአምልኮ ደረጃን እየሰጡ የመኻዝ ዓላማቸውንና ተግባራቸውን፡ አጠናክረው እንደቀጠሉበት፡ በሚገባ አውቀነው ነው።

ደግሞም፡ እግዚአብሔር፡ ወንድና ሴት አድርጎ፡ በመልኩ የፈጠረውን ሰው፡ ጥንትም፡ በአዳምና በሔዋን፥ ኋላም፡ በመልከ ጼዴቅ፥ በመጨረሻም፡ ራሱ፡ ከኢትዮጵያዊቷ ድንግል፡ ከቅድስት ማርያም ሰው ኾኖ በመወለድና በማገልገል፥ አርአያ በመኾንና በማስተማር፥ ቤዛ ኾኖ በመሠዋትም፡ በዘርና በቀለም፥ በቋንቋና በኑሮ ደረጃ፥ በእውቀትና በሀብት ይዞታ፥ በሃይማኖትና በክህነት፥ በሥልጣንና በኃይል፥ በክብርና በሥርዓተ መንግሥት፥ በሥጋዊውና በመንፈሳዊው፥ በሰላምና በፍቅር፡ ፍጹም አንድ ያደረገው መኾኑን አውቀን ነው።

እውነታው፡ ይህ ኾኖ ሳለ፡ የኾነውና እየኾነ ያለው ግን፡ ሓሰቱ ነው። አዎን! ፈጣሪው፡ እንዲህ አድርጎ፡ በኹሉም ዘርፍ፡ አንድ ያደረገውን፥ ለእውነተኛ እግዚአብሔራዊ መልኩም፡ ማለትም፡ ለአግዓዚነት፥ ወይም፡ ለዐም-ሓራነት፥ ወይም፡ ለቅዱሱ ኪዳን ክርስቲያንነት፥ በአጠቃላይም፡ ለፍጹሙ ኢትዮጵያዊነት ያበቃውን፡ ያን ሰብአዊ ፍጡሩን፡ በተለይ፡ ይኼ፡ ኢትዮጵያዊው ትውልድ፥ የቀረውን ሰብአዊ ትውልድ ጨምሮ፡ ራሱንና ሌላውን፡ እርስ በርሱ ለያየ። የርኩስ መንፈስ አምልኮንም፡ በድፍረትና በገሃድ፡ በመካከሉ አስፋፋ። ይህንም የሚያደርገው፡ ጠንቀኛ በኾነው፡ በሰይጣናዊው የክፋት ፍልስፍናና አመራር፥ አሠራርና አፈጻጸም መኾኑ፡ በኹሉ ዘንድ የሚታወቅ ነው።

እንግዴህ፡ በዚች፡ በዘንድሮዋ ጾመ ኢትዮጵያችን አማካይነት፡ ከዚህ ቀጥሎ ተስፋፍቶ በቀረበው ሓተታ እንደሚነበበው፡ በእኛ በኩል የሚጠበቅብንን፡ የቅዱሱን ኪዳን ኢትዮጵያዊ ግዳጅ የምንፈጽም መኾናችንን እያረጋገጥን፡ ይኼው፡ ኢትዮጵያዊው ትውልድ፡ በቤተ ሕዝቡ፥ በቤተ ክህነቱና በቤተ ምልክናው አማካይነት፡ በቅዱሱ ኪዳን ላይ እያካኼደው ካለው፡ የክህደትና የዓመፅ፥ የምንዝርናና የኃጢአት ተግባሩ፡ በእውነተኛ ንስሓ እንዲመለስ፡ ይኸው ደጋግመን፡ እናሳስበዋለን።

## ለኢትዮጵያዊው ችግር፡ ኢትዮጵያዊው መላ!

እውነታው፡ ይኼ ከኾነ ዘንድ፡ ታዲያ! ይህ ትውልድ፡ ይህን ኢትዮጵያዊ ችግር፡ ለመፍታትና ለማስወገድ የሚቻለው፡ እንዴት ነው? ለዚህ፡ ምን ዓይነት ሌላ አማራጭ ዘዴ ይኖረዋል? ከሌለውስ፡ "የለኝም!" በማለት፡ ዝም ብሎ ሊቀመጥ፥ ወይም፡ ሊመለከት ይገባዋልን? አይደለም! ለቃል ኪዳን ፈጣሪያችን፡ ምስጋና ይድረሰውና! ትውልዱ፡ በንስሓ ለመመለስ ፈቃደኛ ከኾነ፡ በሌላኛው፥ በሰውኛው መንገድ፡ የማይቻለው ኹሉ፡ በቅዱሱ ኪዳን ምክንያት፡ በኢትዮጵያዊው ዘንድ እንዲቻል ስላደረገው፡ ኢትዮጵያዊው ትውልድማ፡ እንዲህ ብሎ፡ በተስፋ መቍረጥ፡ ወደኋላው ሊያፈገፍግ አይገባውም።

እንግዴህ፡ ይኸው ትውልድ፡ ይህን ኢትዮጵያዊ ችግሩን፡ እንዴት አድርጎ፡ በቀላሉና በፍጥነት፥ በጸጥታና በወግ ለመፍታትና ለማስወገድ፥ ከዚህ የተነሣም፡ ክፉው ጊዜ አልፎለት፡ የሚመኘው፡ ደጉና ደኅናው፥ የሰላሙና የብልጽግናው ዘመን፡ በቶሎ እንዲመጣለት ለማድረግ እንደሚችል፡ እናመለክተው ዘንድ፡ እስኪ ይፍቀድልን!? ትውልዱ፡ ይህን ችሮታ የሚጠየቀው፡ እስከዛሬ፡ ለባዕዳኑና ለተቃዋሚዎቹ፥ ለወዳጅ ጠላቶቹ ሳይቀር፡ አለቁጥጥር፡ ልቅ አድርጎና አትረፍርፎ የለገሠውን ፈቃደኝነቱን፡ አኹን፡ ለእኛ፡ ለወገኖቹ፡ ቆጥቦም ቢኾን፡ ለአንዴ ለመስጠት፡ ምንም ቢኾን፡ "አይነፍገንም!" ብለን በማመን ነው፤ ትውልዱ፡ ይህን በማድረጉ፡ የአገሩንና የወገኑን፥ የራሱንም ደኅንነት፡ የቱን ያህል እንደጠቀመ፡ የኋላ ኋላ፡ ያስተውለዋል።

በዚህ መልክ፡ ፈቃዱን ካገኘን፡ ለዚሁ፡ ለኢትዮጵያዊው ችግር ማስወገጃ፡ ለትውልዱ የምናቀርብለት የመፍትሔ አሳብ፡ "ያገሩን ሠርዶ፡ ባገሩ በሬ!" እንዲሉ፡ በዘበናዮች ዘንድ የተናቀውን፡ "ኢትዮጵያኛውን መላ" መኾኑን፡ ስናበሥር፡ ደስ ይለናል።

“ኢትዮጵያኛው መላ” ያልነውም: በይፋ ታውቆ የኖረው የባዕዳኑ ፈሊጥ: በምንም ዓይነት ያልተቀላቀለበትን፥ ፍጹም ንጹሕና አገር-በቀል የኾነውን እንጂ: አዲስ፥ ወይም: እንግዳ የኾነውን አይደለም፤ ኢትዮጵያውያን: ከጥንት ጀምረው: ለአያሌ ሺህ ዓመታት: እንደዛሬው ዘመን: በግልም ኾነ: በአገር ደረጃ: ማናቸውም ዓይነት ችግር ሲገጥማቸው: ያን ችግር ፈትተው: እያስወገዱ የኖሩበትን ማለታችን ነው፤ ይኸው ችግር: በአኹኑ የኢትዮጵያ ትውልድና በባዕዳኑ ሰዎች ዘንድ: እንዲህ: መፍትሔ ያጣና ግራ የሚያጋባ፥ በምሥጢር የተተበተበም በሚኾንባቸው ጊዜ: የተጠቀሙበትን፥ ዛሬም ፈትተው: ሊያስወግዱ የሚችሉበትን: ልዩ የብልህነት ዘዴያቸውን ነው: እኛ: “ኢትዮጵያኛው መላ” ያልነው::

በመሠረቱ: <u>*“ችግር”*</u> የሚባለው: የሕይወት ጠንቀኛ ጣጣ: እንደክፋት፥ እንደኃጢኣትና እንደሞት ኹሉ: በራሱ: በሰው ፍላጎት የመጣና የሚመጣ እንጂ: ጥንት: በተፈጥሮ: የህልውና አካል ኖሮት: የተከሠተ ኾኖ አይደለም፤ ቀድሞውኑም ቢኾን: ችግርን: ፈልጎ ያመጣው: ከቀዳማውያኑ አዳምና ሔዋን ጀምሮ: እስከዛሬ ድረስ: ራሱ ሰው መኾኑ ተጽፏል፤ ይታወቃልም። ያው ሰው ደግሞ: ሲፈልግ: ያንኑ: ፈልጎ ያመጣውን ችግር: ራሱ መልሶ ሊያስወግደው ችሎ እንዳስወገደው፥ ለኹልጊዜም ሊያስወግደው እንደሚችልም: እስከዛሬና ለዘለዓለም: የተረጋገጠ እውነታ ኾኗል::

ይህም ሊኾንና ሊደረግ የተቻለው: ከዳግማዊቷ ሔዋን: ከድንግል ማርያም ከተወለደው: ከዳግማዊው አዳም: ከኢየሱስ ክርስቶስ ጀምሮ: በእርሷ: ለአምላክ እናትነት መብቃትና በእርሱ: በተፈጸመው የትስብእት ቤዛነት፥ ከዚህ የተነሣም: ለቀረው ሰው ኹሉ በተሰጠው ጸጋ ነው። ስለዚህ: በአኹኑ ጊዜ የተንሰራፋውን ኢትዮጵያዊ ችግር: ፈልጎ ያመጣው: ራሱ: ይህ: ኢትዮጵያዊ ትውልድ እንደመኾኑ መጠን: ይኸው ኢትዮጵያዊ ትውልድ: ከፈለገ ደግሞ: ይህንኑ: ከዓቅሙ በላይ የኾነበትንና በሰውኛው ዘዴ ሊያስወግደው ያልቻለውን: ኢትዮጵያዊ ችግሩን: ራሱ: መልሶ: ሊያስወግደው እንደሚችል: ሊገነዘበው ይገባል:: አዎን! የሚያስወግደውም: በ“ኢትዮጵያኛው መላ” ብቻ ነው::

የፍጡር አካል: በሥጋው: ሕያው ኾኖ ሊንቀሳቀስ፥ ሊሠራና ሊኖር የሚችለው: በነፍስ: የኃይል ምንጭነት መኾኑ፥ ደግሞም: ሰው የሠራው ሠረገላ እንኳ: በመንቀሳቀስ ሊያገለግል የሚችለው: በዚያው: በሠሪው: በሰው ተቆጣጣሪነት መኾኑ ይታወቃል:: እንደዚሁ ኹሉ: አንድን ግለሰብ፥ አንድን ቤተሰብ፥ አንድን ኅብረተሰብ፥ ወይም: አንድን ሕዝብ: አስማምቶና አዋሕዶ የሚያኖረው፥ የሚያንቀሳቅሰውና የሚያሠራው: አንድ ኃይል ሊኖረው: የግድ ያስፈልጋል፤ ሌላ አማራጭ የለም፤ አለዚያ: ያ ግለሰብ፥ ያ ቤተሰብ፥ ያ ኅብረተሰብ፥ ወይም: ያ ሕዝብ: ሕያው የኾነ: ህልውናን አግኝቶ: በዚያ ሕይወት ሊቀጥል አይችልም:: ያም ኃይል: <u>ሃይማኖት</u> ነው:: የዚያ አካል: ህልውናው: መልካምና ፍሬያማ እንዲኾንለት ከተፈለገ ደግሞ: ያ ሃይማኖት: <u>ፍጹምና ንጹሕ እውነት መኾን</u> ይኖርበታል::

ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያውያን፡ ለህልውናቸው፡ ታላቅ አገልግሎትን ያበረከተላቸው ኃይል፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊው ተዋሕዶ ሃይማኖታቸው መኾኑን ለማስተባበል፡ ከቶ አይቻልም፤ እርሱም፡ በፍቱን መሣሪያነቱ፡ ለችግራቸው ማስወገጃ አድርገው ለሚጠቀሙበት፡ ለ"ኢትዮጵያኛው መላ" ጥሩ ምንጭ ኾኗቸው ኖርዋል፡፡ ነጻነታቸውን በማስገኘቱ፥ ይህንኑም ነጻነት፡ ለ፯ሺ፫፻፺ ዓመታት አጽንቶና አረጋግጦ፡ እስከዛሬ በማቆየቱ ረገድ፡ ሙሉና የብቻው የኾነ ድርሻ ያለው፡ ይኸው ሃይማኖታቸው ነው፤ ለዚህም፡ እንደዐለት ድንጋይ ጸንቶና ነዋሪ ኾኖ ከሚመሰክረው፡ ከራሱ ሐውልትነት የበለጠ፡ ሌላ ማስረጃ አያስፈልገውም፡፡

እንዲህ ከኾነ፡ ከፍጥረት መጀመሪያ አንሥቶ፡ እስከዛሬ የኖረውን፥ በሕያውነቱም፡ ለዘለዓለም የሚቀጥለውን፡ ይህን የመሰለውን ፍቱን መሣሪያ፡ የዘመኑ ኢትዮጵያዊ ትውልድ፡ በጊዜው ለተጋረጠበት ኢትዮጵያዊ ችግር ማስወገጃ አድርጎ ሊጠቀምበት እንደሚገባ፡ እሙን ነው፡፡ ነገር ግን፡ ይኸው ኢትዮጵያዊ ትውልድ፡ ለመልካምና ለዘለቄታ ህልውናው፡ መሠረትና ማንቀሳቀሻ የኾነውን፡ ይህን ፍቱን ኃይል፡ መሣሪያ አድርጎ ሊጠቀምበት አልፈለገም፤ ባለመፈልጉም፡ እነሆ፡ ችግሩ፡ እየጸናበት ከመኼድ በቀር፡ የተሻለ ነገር ሊመጣለት የማይቻል ኾኖ ቆየ፡፡ የዚህን እውነታ ለማረጋገጥ፡ ወደሩቅ ዘመን መኼድ ሳያስፈልግ፡ እስከዛሬ፡ ለአርባ ዓመታት ያህል ለኾነ ዘመን፡ የቀጠለውንና እየባሰ የኼደውን፡ ይህንኑ ችግር፡ በተጨማሪ ማስረጃነት ማቅረቡ ብቻ የሚበቃ ይኾናል፡፡

"ኢትዮጵያኛውን መላ" ከመግለጻችን በፊት፡ በትውልዱ ልበ-ደንዳናነትና እምቢተኛነት ምክንያት፡ ዛሬ ያለው የኢትዮጵያ ችግር፡ ተንሰራፍቶ በመቀጠሉ፡ ብዙዎችን የእውነት ሰዎች ሳይቀር፡ አሳዝኖ፡ ተስፋ ወደማስቆረጡ፥ ዓመፀኛውንና ከሃዲውንም፡ "እስከማስለቀስና ጥርስ ማፋጨት" ማድረሱን በተመለከትን ቊጥር፡ ገልጠን በማንበብ፡ የምንጠናከርበት፡ አንድ መጽሓፍ አለ፤ እርሱም፡ ዓለም፡ በእውነተኛነቱ የተቀበለው፡ ቅዱሱ መጽሓፍ ነው፤ በዚያ የተመዘገበውን፡ እንዲህ የሚለውን፡ የባለራእዩን ቃል፡ ለትውልዱ መጽናኛ ይኾን ዘንድ፡ እዚህ ላይ፡ እነሆ፡ አስቀድመን ጠቅሰነዋል፡-

**"በውስጥና በውጭ የተጻፈባት፥ በሰባት ማኅተም የታተመች መጽሓፍ፡ በዙፋኑ ላይ በተቀመጠው፡ በቀኝ እጁ ተይዛ፥ ታላቅ መልአክም፡ 'ያችን መጽሓፍ ሊከፍት፥ ማኅተሟንም ሊፈታ፡ የሚገባው ማነው?" እያለ፡ በታላቅ ድምፅ ሲያውጅ አየሁ፡፡ ያችን መጽሓፍ ለመክፈት፥ ለማየትም የተቻለው፡ በሰማይም ቢኾን፥ በምድርም ቢኾን፡ ማንም አልተገኘም፡፡ ያችን መጽሓፍ፡ ሊከፍታት፥ ሊያያትም የሚገባው፡ ማንም ስላልተገኘ፡ ብዙዎች አለቀሱ፤ እኔም አብሬአቸው አለቀስሁ፡፡**

**"በእዚያ ከነበሩት አለቆች መካከል፡ አንዱ፡ እንዲህ አለኝ፡- 'ኢትብኪ! ናሁ፡ ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ፥ ዘእምውስተ ሥርዉ ለዳዊት፥ ከመ ይፍትሓ ለይእቲ መጽሓፍ፥ ወለማኅተሚሃ!'" ይህም፡ "'አታልቅስ! እነሆ፡ ከዳዊት ሥር፥ ከይሁዳ ወገን የኾነ አንበሳ፡ ይህችን መጽሓፍ ይገልጥ ዘንድ፥ ማኅተሟንም ይከፍት ዘንድ፡ ድል ነሥቷል!'"** ማለት ነው፡፡ (ራእ. ፭፥ ፩-፭፡፡)

በዚህ ቃል መሠረት፡ *"ችግር"፡* ከእግዚአብሔር አብና ከኢትዮጵያዊቷ ድንግል ማርያም በተወለደው፡ በኢትዮጵያዊው ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ድል አድራጊነት፡ ለአንዴና ለመቼውም ጊዜ ተፈትቶ ተወግዷል፤ እንዲህ ኾኖ መወገዱ፡ ተረጋግጦ ከታወቀ፡ እንግዴህ ወዲህ፡ ከእያንዳንዱ፡ ከትውልዱ አባል የሚጠበቀው ድርሻ፡ ተስፋ በመቍረጥ፡ "ማልቀስና ጥርስ ማፋጨት" ሳይኾን፡ በዚህ ዜና፡ ደስ በመሰኘት፥ በተገኘውም ጸጋ በመጠቀም፡ የየግል ግዳጅን ለመፈጸም መዘጋጀት ነው፡፡ የዚህ ዝግጅት፡ መነሻና መድረሻ፡ ምን እንደኾነ፥ እንዴትስ፡ መካኼድና መከናወን እንዳለበት፡ ለትውልዱ እናመልክት!

በረቂቅ ኃያልነቱና በፍቱን መሣሪያነቱ የሚታወቀው፡ "ኢትዮጵያኛው መላ"፡ ለኢትዮጵያውያን፡ በቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖታቸው አማካይነት፡ ከፈጣሪያቸው የተሰጣቸው፡ ልዩ ጸጋ ነው፤ ሌላ ማማረጫ ሳያስፈልገውም፡ ከዚህ ዘመን ደርሷል፤ እርሱንም፡ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ በማሰብ፥ በመናገርና በማድረግ ሲጠቀሙበት፥ በነፍስ፥ በሥጋና በመንፈስም ሲፈጽሙት፡ እስከዛሬ ኖረዋል፡፡

ታዲያ! ለኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ የመፍትሔ ኃይል ያለው ረቂቅ መሣሪያቸው የኾነው፡ ይህ፡ "ኢትዮጵያኛው መላ" ከቶ ምንድር ነው? "ኢትዮጵያኛው መላ"ማ፡ በ<u>"ጾመ ኢትዮጵያ"</u> የተከሠተው፡ ሃይማኖታዊው ምግባራቸው ነው፡፡ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ ሥጋዊ ዓቅማቸው በሚፈቅድላቸው መጠን፡ ለሦስት ቀናት፡ በጽሙና የሚጠመዱበት፡ የንስሓ ጾም፥ ጸሎትና ምጽዋት ነው፡፡

"ጾመ ነነዌ" እያልን፡ በያመቱ፡ በልማድ ብቻ ስንጾማት የኖርነው፡ የሦስት ቀኖች ጾማችን፡ እንዳለፉት ዓመታት፡ ዘንድሮም፡ "ጾመ ኢትዮጵያ" ብለን፡ እንጾማት ዘንድ፡ አገራችን ኢትዮጵያ፡ እርሷም፡ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ የአምላክ እናት፡ በስሟ ያቀረበችልን፡ ታላቁ ጥሪዋ ነው፡፡ ሲጠራቀምና ሲከማች ኖሮ፡ በ፲፱፻፷፯ ዓ.ም. የፈነዳውን፥ ከየራሳችንም የጀመረውን፡ ይህን፡ የዛሬውን፡ አገራዊና ሕዝባዊ ችግራችንን ለማስወገድ እንዲያስችል፡ መልካም አጋጣሚ ኾኖ፡ ለኢትዮጵያውያንና ለኢትዮጵያውያት የቀረበው፡ "ኢትዮጵያኛው መላ"፡ <u>"ጾመ ኢትዮጵያ"</u> ነው፡፡

አዎን! በእርግጥ፡ ስለአገራችንና ስለእየራሳችን፥ ስለወገኖቻችንና ስለዓለሙም፡ በተለየ ሃይማኖታዊ ትኵረትና መንፈሳዊ ተመስጦ ተዘጋጅተን፡ በግልና በኅብረት ልንጾማት የሚገባን፡ የኢትዮጵያ ጾም ናት፡ ይህች፡ የ"ኢትዮጵያኛው መላ" ፍቱን ኃይልና መሣሪያ፡፡

እንግዴህ፡ አገራችን ኢትዮጵያ፡ በስሟ ያቀረበችልንን፡ ይህን ታላቅና ልዩ ጥሪ፡ በሙሉ ፈቃድ የምንቀበለው ከኾነ፡ ይህ መልእክት፡ በማናቸውም መንገድ፡ ከእያንዳንዳችሁ ዓይን፥ ጆሮ፥ ወይም፡ እጅ፡ ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ፥ በተለይም፡ በመጨረሻ፡ <u>ከሰኞ፡ ጥር ፳፭፡ እስከረቡዕ፡ ፳፯ ቀን፥ ፳፻፯ ዓ. ም.</u> ባሉት ሦስት ቀኖች ውስጥ፡ በምግባር ላይ ውሎ እስከሚፈጸምበት ዕለት ድረስ፡ የ"ጾመ ኢትዮጵያ"ን ሥርዓት፡ በንጹሕ ኢትዮጵያዊነታችን ተከትለን፡ ለመልካሙ ፍሬ እናበቃው ዘንድ እናሳስባችኋለን፡፡

ይህ ሥርዓት፡ አባቶቻችንና እናቶቻችን፡ በየቤታቸው ተወስነው፣ የነፍስ፣ የሥጋና የመንፈስ ጫማቸውን አውልቀው፣ ከአልጋ ወርደውና ተለይተው፣ በምድርም ላይ ወድቀው፣ እየራሳቸውን፡ በእውነተኛው ኢትዮጵያዊ የንስሓ መንፈስ አንጽተውና አጽንተው፣ ኹሉን በሚያውቀው ፈጣሪያቸው ፊት፡ የውጭና የውስጥ ኹለንተናቸውን ገላልጠው የሚያቀርቡበት ነው፡፡ እኛ፡ የዛሬዎቹ ልጆቻቸው፡ የእነርሱን ፈለግ በመከተል፡ እያንዳንዳችን፡ በያለንበትና በየተግባራችን ተወስነን፣ በቀናች ሃይማኖትና በትክክለኛው ምግባር ተጠምደንም፡ በቅድሚያ፡ እየራሳችንን፡ ከራሳችን፣ ከሰውና ከእግዚአብሔር ጋር፡ በንስሓ የምናስታርቅበት ነው፡፡ ቀጥለንም፡ በየግል ሰውነታችንና እርስ በርሳችን፡ በመንፈስ ቅዱስ፡ አንድ ኾነን፡ ከፈጣሪያችን ጋር፡ በእውነተኛው አምልኮ የምንገናኝበት ነው፡፡

ይህን ካደረግን፡ እኛ፡ የዛሬዎቹ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ ከእየራሳችንና ከአምላካችን፣ ከወገናችንም የሚፈለግብንን፡ የመጨረሻ ግዳጅ መፈጸማችን ነውና፡ ለዛሬው ችግራችን፡ መፍትሔ የሚኾነንን ምሕረት፡ በእርግጥ፡ ከእርሱ፡ ከፈጣሪያችን እናገኛለን፤ ማግኘታችንንም፡ ከእርሱ ወርዶ የሚያድርብንና ኹሉን የሚገልጽልን፡ ቅዱሱ የእውነት መንፈስ፡ ራሱ፡ ያሳውቀናል፤ **“ኢትዮጵያ፡ እጆቿን፡ ወደእግዚአብሔር ትዘረጋለች!”** የሚለውን መለኮታዊ መመሪያችንን፡ በሥራ ላይ ማዋላችንንም፡ ያስረዳናል፤ የኢትዮጵያኛው መላችን አካላት የኾኑትን፡ እነዚህን፡ ጾምን፣ ጸሎትንና ምጽዋትን፡ አጠቃልሎ የያዘውን፡ ሃይማኖታዊ ምግባራችንን፡ ለንስሓ ፍሬ ማብቃታችንን ያበሥረናል።

በፍጻሜውም፡ ይህን የምንሻውን፡ መለኮታዊ ምሕረት፡ በግልና በአገር ደረጃ፡ ለእኛ ብቻ ሳይኾን፡ ከዚያም አልፈን፡ ለዓለሙም ጭምር፡ በሚያስተማምን መልኩ ለማስገኘት መቻላችንንም ያስገነዝበናል፡፡

ከሦስቱ ቀኖች ጾማችን፡ የሚጠበቀው ፍሬያማ ውጤት የሚገኘው፡ ከላይ የተጠቀሱት ዕለታት ደርሰው፡ ሱባኤው በሚፈጸምበት ጊዜ ብቻ አይደለም፤ ነገር ግን፡ ገና ከወዲሁ፡ የዚህ ሃይማኖታዊና መንፈሳዊ ሰልፍ ዝግጅት፡ ዜናው መሠራጨት ጀምሮ፡ መልእክቱ፡ ከእያንዳንዳችሁ ዓይን፣ ጆሮ፣ ወይም፡ እጅ ሲደርስ፡ ውጤቱን፡ በአንዳንድ ምልክቶች ተከሥቶ ታገኙታላችሁ፡፡ ከእነዚህም ምልክቶች መካከል አንዱ፡ የዚህ ችግራችን ክፉ ምንጭና አበጋዝ የኾነው ዲያብሎስ፡ ከነሠራዊቱ፡ ማለትም፡ አጋንንቱና ሰብአውያን አገልጋዮቹን ጨምሮ፡ በመበርገግ፡ ከሚደርስበት ጭንቀትና ጥበት የተነሣ፡ የሚያደርገው መወራጨትና መታወክ ነው፡፡

በዚህ ጊዜና በዚህ አንጻር፡ በእኛ በኩል፡ ሊታይ የሚገባው፡ በጎ ምልክት ደግሞ፡ በእግዚአብሔር መንፈስና በእውነተኛ አምልኮ ኾነን በምንፈጽመው፡ በዚህ የጾም፣ የጸሎትና የምጽዋት ምግባራችን ምክንያት፡ በውስጣችን የሚሰማን፡ መታመንና በውጫችን የምናሳየው፡ እርጋታ ይኾናል፡፡

## የጾመ ነነዌ እና የጾመ ኢትዮጵያ ውሕደት

በኣኹኑ ጊዜ የተከሠተውና የተፈጸመው፡ ይህ፡ የ"ጾመ ነነዌ" እና የ"ጾመ ኢትዮጵያ" ጥምረትና ትሥሥር፡ በሥራ ላይ እንዲውል የኾነው፡ ያለምክንያት አለመኾኑ ሊታወቅ ይገባል፤ በመጨረሻው ዘመን፡ ከፍጥረተ ዓለሙ ጋር ሊፋረዱ፡ በእግዚአብሔር ችሎት ፊት የሚቀርቡት፡ የነነዌ ሰዎችና የኢትዮጵያ ሕዝብ በመኾናቸው ነው፤ የነነዌ ሰዎች፡ በነቢዩ ዮናስ ስብከት፡ እየራሳቸውን፡ ለእውነተኛ ንስሓ በማብቃታቸው፡ የፈጣሪን ምሕረት አግኝተው፡ ከመደምሰስ ድነዋል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ደግሞ፡ በአምላካቸው በእግዚአብሔር፡ የሚያምን፥ የጥበብ ጸጋንም የሰጠው፡ "ሰሎሞን!" የተባለ፡ የአይሁድ ንጉሥ፡ በኢየሩሳሌም፡ ለእግዚአብሔር፡ ቤተ መቅደስ፡ እያሳነፀ መኾኑን፡ በዝና ስለሰሙ፡ ያን ዜና፡ በዓይኖቿ አይታና እውነታውን አረጋግጣ ትመለስ ዘንድ፡ ንግሥታቸው ማክዳ፡ ከአገራቸው፡ ከኢትዮጵያ ምድር ተነሥታ፡ ወደኢየሩሳሌም እንድትጓዝ አድርገዋል፡፡ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ያለውን፡ የዚህን ዝክረ ነገር የሚያወሳው ቃል፡ እዚህ ላይ ሊጠቀስ፡ አግባብ ይኾናል፦

***"ከጻፎችና ከፈሪሳውያን መካከል፡ ሰዎች መጥተው፡ 'መምህር ሆይ! ከአንተ፡ ምልክት ልናይ እንወድዳለን፤' አሉት፡፡ ጌታችን ኢየሱስም መልሶ፡ 'ከዳተኛዪቱ፥ ዓመፀኛዪቱና አመንዝራዪቱ ትውልድ፡ ምልክትን ትሻለች፤ ነገር ግን፡ ከነቢዩ፡ ከዮናስ ምልክት በቀር፡ ምልክት አይሰጣትም፡፡ ...የነነዌ ሰዎች፡ በፍርድ ቀን ተነሥተው፡ ይህችን ትውልድ ይፋረዷታል፤ ያሳፍሩዋታልም፤ በዮናስ ስብከት፡ ንስሓ ገብተዋልና፤ እነሆ፡ ከዮናስ የሚበልጥ፡ ከዚህ አለ፡፡***

***"ንግሥተ አዜብ፡ በፍርድ ቀን ተነሥታ፡ ከዚች ትውልድ ጋር ትፋረዳለች፤ ታሳፍራታለችም፤ የሰሎሞንን ጥበብ ትሰማ ዘንድ፡ ከምድር ዳርቻ ተነሥታ መጥታለችና፤ እነሆ፡ ከሰሎሞን የሚበልጥ፡ ከዚህ አለ፡፡'"*** (ማቴ. ፲፪፥ ፴፰-፵፪፡፡)

ከዮናስና ከሰሎሞን የሚበልጠው፡ ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገረውን፡ ይህን መለኮታዊ እውነታ፡ ለዛሬው የኢትዮጵያ ትውልድና ለዓለሙ ኅብረተሰብ ለማረጋገጥ፡ ወደሩቁ የዜና መዋዕል መዝገብ፡ ተመልሶ ኼዶ መመራመር አያስፈልግም፤ የቅርቡን፡ የኹለተኛውን የዓለም ጦርነት ዝክረ ነገር፡ አገላብጦ ማዘከር ይበቃል።

አዎን! የዚያን ጊዜዎቹ፡ የኢትዮጵያ ትውልድ መሪዎችና የዓለሙ ኃያላን መንግሥታት፡ ቀድሞም ኾነ ዛሬ፡ ኢትዮጵያን፡ ማን እንደኾነች፡ ጥሩ አድርገው ያውቋታል፤ የህልውናዋ መሠረትና የህብቷ መዝገብ፥ የጥበቧ ምንጭና የኃይሏ መጋቢ በኾነው፡ በፈጣሪዋ ከመተማመን በቀር፡ ያለማረሻ፡ ምንም ነፍጥ (የሚተኮስ ጦር መሣሪያ) የሌላት፥ የእግዚአብሔርና የቅድስት እናቱ ስም፡ የሚቀደስባት፥ መንግሥቱ፡ በይፋ የሰፈነባትና የቃል ኪዳን ቅርሶቹ የሚጠበቁባት፥ ሕዝቡም፡ በትንሹ፡ "በቃኝ!" ብሎ፡ በመንፈሳዊ ትሕትና የሚኖርባት መኾኗን፡ ለራሳቸው ተገንዝበው፡ ለሌላውም ጽፈው ያስረዳሉ፡፡

ይኹን እንጂ: በዚያን ጊዜ: እርሷን: ለዘር ጠላቷ: በክህደት አሳልፈው በመስጠት አፈራርሰው: እነርሱ: በሰላም የሚኖሩ መስሏቸው: በኢትዮጵያ ላይ በፈጸሙት ታላቅ በደል: እኒያ መሪዎችና ኃያላን: ከነቃል ኪዳናቸው፥ በጄኔቫ ከተማ ተቋቁሞ ይሠራ ከነበረውም: የመንግሥታት ማኅበራቸው ጋር: የደረሰባቸው ፍጻሜ፥ አዎን! ለዚያ ደባቸውና ክህደታቸው: በናዚ ጀርመን፥ በፋሺስት ኢጣልያንና በተስፋፊዋ ጃፓን አምባገነን ጦረኞች: የተከፈላቸው የፍርድ፥ የበቀልና የቅጣት ዋጋ አይዘነጋም::

እነዚያ ኃያላን: ዛሬም እንደገና: የዘመኑን: የኢትዮጵያ ትውልድ መሪዎችና የተባበሩት መንግሥታት ድርጅታቸውን ይዘው: የቀድሞውን የመሰለ ደባቸውን: በኢትዮጵያና በሕዝቧ ላይ: ያለኃፍረትና ያለይሉኝታ ሲያካኺዱ: ይኸው ይታያል:: ይኹን እንጂ: ይህ ክፉ ግብራቸው: እንደዚያን ጊዜው ኹሉ: በመለኮታዊው ነደ እሳት ለመጫወት እንደመሞከር የሚያስቆጥራቸው መኾኑን አስተውለው: ከዚህ ድርጊታቸው ይታቀቡ ዘንድ: ያለፈው ዝክረ ነገር: የማስጠንቀቂያ ደወሉን በማሰማት: እነሆ: እነርሱንም፥ የዛሬውን የኢትዮጵያ ትውልድም: ያለማሠለስ: ያሳስባቸዋል።

ነገር ግን: ኹሉም: ደወሉን ያዳመጡት አይመስልም፤ ባለፈው ጊዜ: ከታላቁ የእውነት ዳኛ: በየድርሻቸው የተሰጣቸው የፍርድ ጽዋ: ትምህርት ኾኗቸው: ካኹኑ ጥፋታቸው ተጸጽተው: ሊመለሱ አልተቻላቸውም:: ለ“ጾመ ኢትዮጵያ”: መነሻ የኾነውም: ይህ: አደገኛ ኹኔታቸው ነው:: እየራሳቸውን: ከባሰ ቅጣት ለማዳን ሲሉ: ይህን: ብርቱ የህልውናቸውን ጉዳይ: እንደገና እንዲያስቡበት: ኃያላኑን ለማንቃት ነው:: በዛሬው የቅጣት ማዕበል ተጥለቅልቆ ሊዋጥ የሚንገላታውንም ኢትዮጵያዊ ትውልድ ለማትረፍ ነው:: <u>አዎን! የጥንት ፍጡራንን ከደመሰሰው የጥፋት ውኃ: ስምንት ሰዎችን እንዳተረፈችው: እንደኖኅ መርከብ: ይህች ጾም ተዘጋጅታ ቀርባለች::</u>

ነገርን: ነገር ያነሣዋልና: ልክ የዛሬ አምስት ዓመት: ይህችኑ ጾም በሚመለከት: አንድ: ድንገተኛና አስደንጋጭ የኾነ ድርጊት በመድረሱ ምክንያት: "**ይድረስ፡- ለቅዱስ ኪዳኗ የኢትዮጵያ ልጆች!**" በሚል አርእስት: በዚሁ የጎዋ ሰሌዳችን ዋና ገጽ ላይ ያስተላለፍነው መልእክት መኖሩን: እዚህ ላይ: ልናስታውሳችሁ እንወድዳለን።

ያም: ቀድሞ: በዘልማድ: "ጾመ ነነዌ" እያልን ስንጾማት የኖርነውን: ይህችኑ: የጊዜያችንን ጾመ ኢትዮጵያን: ሥርዓቷን መፈጸም: በጀመርንባት እኩለ ሌሊት ላይ: በቀጥታ: ነነዌንና ኢትዮጵያን የነካ፥ ልዩና እንግዳ የኾነ: አንድ የደወል ድምፅ: በዓለሙ ኹሉ: ከጽንፍ እስከ ጽንፍ በመሰማቱ የተላለፈው የመንፈስ ቅዱስ መልእክት ነው። ይኸው መልእክት: ለዛሬው የኢትዮጵያና የዓለሙ ኹኔታ: ፍጹም እውነትና አሳማኝነት ያለው፥ ጆሮን እስከማሳመም የሚደርስ: እጅግ ኃይለኛ የደወል ድምፅ በመኾኑ: እነሆ: እንዳለ መልሰን አቅርበነዋልና: በማስተዋል ተመልከቱት! ቃሉም: እንዲህ የሚል ነው፡-

"በኢትዮጵያ አየር መንገድ ጥያራ ላይ ስለደረሰው አሠቃቂ አደጋ፡ ሰሞኑን፡ በልዩ ልዩ የብዙኃን መገናኛዎች መስመር የተላለፈውን አስደንጋጭ መርዶ፡ ኹላችንም፡ በያለንበት ሰምተነዋል። እግዚአብሔር፡ የሙታኑን ነፍሳት እንዲምር፥ ቋሚዎቹን ኀዘንተኞቹንም እንዲያጽናና እንጸልያለን።

"አደጋው የደረሰው፡-

-ቀድሞ፡ በልማድ፡ "ጾመ ነነዌ"፥ ዛሬም፡ "ጾመ ኢትዮጵያ" እያልን የምንጠመድባትን፡ የሦስት ቀናት ጾማችንን በጀመርንበት፡ ልክ፡ ከእኩለ ሌሊት በኋላ መኾኑ፥

-የጥንቷና ዘመናዊዋ ነነዌ፡ ከነበረችበትና ካለችበት አካባቢ፡ ከዛሬዋ፡ የሊባኖስ መናገሻ ከተማ፡ ከቤይሩት፡ ለበረራ በተነሣ የኢትዮጵያ ጥያራ ላይ መኾኑ፥

-ይህን ኹኔታ፡ ስለጾመ ኢትዮጵያ፡ በጎዋ ሰሌዳችን ላይ ካወጣነው መልእክት ጋር አያይዛችሁ ስትመለከቱት፥

-ደግሞም፡ ከጥቂት ዓመታት በፊት፡ የአንበሳው ምልክት፡ ከኢትዮጵያ አየር መንገድ የይፋ ምልክትነቱ እንዲነሣ መደረጉን በመቃወም፡ እኛ፡ የቅዱስ ኪዳኗ ኢትዮጵያ ልጆች፡ ከእንግዲህ ወዲህ፡ በበረራው የማንገለገል መኾናችንን፡ በይፋ አስታውቀን፡ ለአየር መንገዱ ዋና ሥራ አስኪያሃጅ ከጻፍነውና በጎዋ ሰሌዳችን ላይ ካወጣነው ደብዳቤያችን ጋር፡ ይህንኑ አደጋ ስታገናኙት፡ ምን ዓይነት ስሜትን አሳደረባችሁ?

"ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ስለነነዌ ሕዝብና "ንግሥተ ሳባ" ስለተባለችው፡ የኢትዮጵያ ንግሥት በማጣመር፡ በብሥራተ ማቴዎስ፡ ምዕራፍ ፲፪፥ ቍጥር፡ ፴፰-፵፪ ላይ በተናገረው ቃሉ መሠረት፡ የዛሬዎቹ፡ የነነዌ (የሊባኖስ) እና የኢትዮጵያ ሕዝቦች፡ በአንድነት፡ የሦስቷን ቀን ጾምና ጸሎት፡ ሳይወዱ በግድ፡ በብሔራዊና በመንግሥታዊ ደረጃ፡ በታላቅ ኀዘን ተውጠው በመፈጸም እንዲያሳልፉ ማድረጉ፡ እግዚአብሔር፡ ለእኛ፡ ለአማኞቹ፡ የቅዱስ ኪዳኗ ኢትዮጵያ ልጆች፥ ለቀረውም፡ ለዘመናችን የኢትዮጵያና የዓለሙ ትውልድ፡ "ምን ቍም ነገርን ሊያሳስበን ፈልጎ ነው?" ብለን፡ እየራሳችንን ልንጠይቅ፥ እርስ በርሳችንም ልንጠያየቅ ይገባናል።

"ይህን እውነታ፡ በበለጠ ስናጤነው፡ መልስ እንድንሰጥባቸው የሚያስገድዱን፡ ሌሎችም፡ ሃይማኖታውያን ጥያቄዎች፡ በእርግጥ፡ በውስጣችን ይነሣሡብናል፤ እነዚህም፡ ከላይ በተጠቀሰው፡ በመለኮታዊው የምሥራች ቃል (በወንጌሉ) የተወሱትን፡ ኹለቱን ሕዝቦች ይመለከታሉ። "እኒህም፡-

-በአንድ ወገን፡ በነቢዩ፡ በዮናስ ስብከት፡ እውነተኛውን ሃይማኖታዊ ንስሓቸውን፡ በእውነተኛው የጾም ምግባራቸው፡ እውን አድርገው በመፈጸማቸው፡ የእግዚአብሔርን ፍጹም ምሕረት ለማግኘት የበቁት፡ የነነዌ ሕዝብ ናቸው፤

-በሌላው ወገን ደግሞ፡ በመለኮታዊው ቃል ኪዳን ተወልዶ፡ በእግዚአብሔር አምልኮ ይገኝ የነበረው፡ የባለቃል ኪዳኑ ንጉሥ፡ የዳዊት ልጅ የኾነው ሰሎሞን፡ በኢየሩሳሌም እያካኼደ ያለውን ሃይማኖታዊ ምግባር፡ በዝና የሰሙት የኢትዮጵያ ሕዝብ፡ የመለኮታዊዉን ቃል ኪዳን ዘር እና ለሃይማኖት ደካሞቹ የእሥራኤል ልጆች፡ መሓሪው እግዚአብሔር፡ እርሱን ያመልኩባት ዘንድ፡ ሰጥቷቸው፥ እነርሱ ግን ለዚያ ጸጋ ባለመብቃታቸው፡ ከእነርሱ ተወስዳ፡ ለቅዱስ ኪዳኗ የኢትዮጵያ ልጆች፡ በአደራ የተላለፈችውን፡ ታቦተ ጽዮንን፡ ወደኢትዮጵያ ለመመለስ፡ "ንግሥተ ዓዜብ" የተባለችውን መሪያቸውን ማክዳን፡ ከታላቅ ስጦታና ጓዝ ጋር፡ ወደአባቶቿ፡ ወደእነመልከ ጼዴቅ ከተማ፡ ወደኢየሩሳሌም የላኩት፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ናቸው።

"ታዲያ! በቅርቡ፡ በሓይቲ የደረሰው፡ የምድር መናወጥ ካስከተለው፡ አሠቃቂ መከራ ጋር፡ ያን፡ የቀድሞውንና ይህን፡ የዛሬውን፡ እውን ኹኔታ፡ አገናዝበን ስንመለከተው፡ የብዙዎች ሊባኖሳውያንና ኢትዮጵያውያን ሕይወት በተሠዋበት፡ በዚህ አሠቃቂ እልቂት፡ እግዚአብሔር፡ ለዛሬዎቹ ነነዌዎችና የዓለሙን ትውልድ ለሚወክሉት፡ የሊባኖስ ሕዝብ፥ ይልቁንም፡ የደቡቧን ንግሥት፥ እርሷም፡ ድንግል ማርያምን ለምትወክለው ኢትዮጵያ፡ "ሕዝቧም፥ ልጆቿም ነን!" ለምንለው፡ ለእኛ፡ መልእክቱ፡ ከቶ ምንድር ነው?

"ወይስ፡ ይህ ኹሉ፡ ለምን እንደኾነ የሚያውቀው፡ እርሱው፡ ፈጣሪያችንና መድኃኒታችን፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ዛሬም፡ በመንፈስ ቅዱስ፡ **"በዚያ ወራት፡ ሰዎች፡ ወደጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መጥተው፡** [በዚያን ጊዜ፡] **ጲላጦስ፡ ደማቸውን፡ ከመሥዋዕታቸው ጋር ስለቀላቀለው፤ ስለገሊላ ሰዎች፥** [በአኹኑ ጊዜም፡ በሓዪቲ አገር በደረሰው የምድር መናወጥና በማዕከላዊው ባሕር ውስጥ በተከሰከሰው፡ በኢትዮጵያ፡ አየር መንገድ ጥያራ አደጋ ምክንያት፡ ስላለቁት ሰዎች] **ነገሩት።**

**"እርሱም መልሶ እንዲህ አላቸው፦ 'ይህች መከራ ስላገኘቻቸው፡ እነዚህ ገሊላውያን** [ሓዪቲያውያን፥ ሊባኖሳውያንና ኢትዮጵያውያን]፡ **ከቀሩት፡ የገሊላ** [የሓዪቲ፥ የሊባኖስና የኢትዮጵያ] **ሰዎች ኹሉ ይልቅ ተለይተው፡ ኃጢአተኞች የኾኑ ይመስላችኋልን? አይደለም፤ እላችኋለሁ! እናንተም፡ ንስሓ ካልገባችሁ፡ ኹላችሁ፡ እንደእነርሱ ትጠፋላችሁ።**

**"ወይስ፡ እነዚያ፡ በሰሊሆም፡ ግንብ ተጭኖ የገደላቸው፡ ዐሥራ ስምንቱ** [እልፍ አእላፋቱ፡ የሓዪቲ፥ ሃምሳ አራቱ፡ የሊባኖስና ሠላሳዎቹ፡ የኢትዮጵያ] **ሰዎች፡ ከቀሩት፡ የኢየሩሳሌም** [የሓዪቲ፥ የሊባኖስና የኢትዮጵያ] **ሰዎች ይልቅ ተለይተው፡ኃጢአተኞች የኾኑ ይመስላችኋልን? አይደለም፤ እላችኋለሁ! እናንተም፡ ንስሓ ካልገባችሁ፡ ኹላችሁ፡ እንደእነርሱ ትጠፋላችሁ።"** የሚለንን ሰምተን ፈጽመናልን? ወይስ፡ ለመፈጸም፡ ገና እያመነታንና እየወላወልን ነን? (ሉቃ. ፲፫፥ ፩-፭።)

"ወይስ፡ "እናምንብሃለን!" ብለን፡ በስሙ ተጠምቀንና ተጠርተን ለምንከተለው፡ የዓለም ክርስቲያኖች፥ በተለይም፡ እየራሳችንን፡ "ኢትዮጵያዊ/ ኢትዮጵያዊት" ብለን፡ ለፍጥረተ ዓለሙ ላስተዋወቅነው ኹሉ፡ ዲያብሎስ፡ ከሺህ ዓመት እሥራቱ፡ ለጥቂት ጊዜ ከተፈታ በኋላ ስለሚኾነው፡ ስለዓለሙ ፍጻሜና ስለኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት፡ ይኸው መሪያችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ያ፡ በቃሉ የነገረንና በራእየ ዮሓንስ ያመለከተን፡ "የእግዚአብሔር ቀን" እየደረሰ ስለመኾኑ፡ ገሃድ የኾነ የማስጠቀቂያ ምልክትን መስጠቱ ይኾን? ወይስ፡ 'ምንን እያመለከተን ነው?' ብለን፡ እየራሳችንን በተመስጦ መጠየቅ የሚያስፈልገን መኾኑን፡ በዚህ አጋጣሚ፡ ኹላችሁንም ልናስታውሳችሁ እንወድዳለን።

"እንግዴህ፡ የአምላክ እናት በኾነችው፡ በኢትዮጵያዋ ድንግል ማርያም፡ የእግዚአብሔር መንግሥትነት፡ እስካኹንና ዛሬ፥ ወደፊትም፡ ለዘለዓለም የምንኖርበትን፡ ይህን፡ የቅዱሱን ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖታችንን በማጽናት፡ በምግባራችን እንጠናከር ዘንድ፡ ይህን መልእክቱን፡ በመንፈስ ቅዱስ ተረድተንና በማስተዋል ተመልክተን፡ የሚገባንን እንድንፈጽም፡ ዕድሉንና ችሎታውን ለሰጠን እግዚአብሔርና ለቅድስት እናቱ፡ ድንግል ማርያም፡ የማያቋርጥ ምስጋናችንን፡ በያለንበት እናቀርባለን።"

## የጾመ ኢትዮጵያ መልእክት ፍሬአማነት፡ እስከምን ድረስ?

ፈጣሪ፡ ይህን የመሰለውን መልእክት፡ በእውንና በግዝፈት አስተላልፎ ሣለ፡ በፍጡሩ ሰው በኩል ግን፡ ይኸው መልእክት፡ ተደማጭነትንና ተቀባይነትን ሳያገኝ በመቅረቱ፡ በኢትዮጵያና በመላው ዓለም፡ መፍትሔ ሳይገኝላቸው የቆዩትን፡ ቀደም ያሉትን የጥፋት ጠንቆች የሚያባብሱ፥ በክፋት ኃይላት እየተጠነሰሱ የሚሠራጩ፡ ሌሎች መርዛማ ድርጊቶች፡ እነሆ፡ ለፍጥረተ ዓለሙ፡ አስፈሪ በኾነ መልክና ይዘት፡ እየተጨማመሩ ሲከሠቱ እናያለን።

አዎን! የነነዌ መታሰቢያ በኾነችው፡ በሊባኖስና በኢትዮጵያ፥ በሃዪቲና በሌሎቹም የነውጥ ክልሎች የነበረው፡ ቀዳሚ ችግር ሳይረግብ፡ በከበደ ኹኔታ በቀጠለበት፡ በአኹኑ ጊዜ፡ ቀደም ብሎ፡ በእስራኤልና በፍልስጥኤም መካከል እየጋመ የቆየው፡ የጦርነት ረመጥና በአፍጋኒስታን እየሰፋ የኼደው፡ የእልቂት አውድማ፥ ከኢራን የሰይፍና ከሰሜን ኮርያ የሰልፍ ምጥ ጣር ጋር ተደማምሮ፡ የዓለሙን ኅብረተሰብ ማስጨነቁ ሳይበቃ፡ በባለሥልጣኖች ዘንድ፡ ጨርሶ ያልተጠበቀ፡ ሕዝባዊ የለውጥ እሳተ ገሞራ፡ ተቀጣጥሎ፡ በቱኒስያ፥ በሊብያ፥ በግብፅ፥ በየመንና በሶርያ፥ ዛሬም፡ ይኸው፡ በዩክሬንና በጠቅላላ፡ በመካከለኛው ምሥራቅ፡ እንደገና ፈንድቶ፥ ነውጡና ዕልቂቱም ቀጥሎ፡ በዓለሙ ኹሉ እያስተጋባ ይገኛል።

በዚህ ረገድ፡ በአንድ በኩል፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ የእግዚአብሔርን መንግሥት መገለጥ፡ ለዓለሙ ኹሉ በማብሠር፡ "ሆሣዕና በአርያም!" እየተባለ፡ በዘለዓለማዊው የንጉሠ ነገሥትነቱና የሊቀ ካህናትነቱ የትሕትና ክብር፡ በአህያ ውርንጭላ ላይ ተቀምጦ፡ ወደኢየሩሳሌም በገባ ማግሥት፡ በእግሩ ሲጓዝ ስለተራበ፡ በመንገዱ አጠገብ ወዳያት፡ ወደአንዲት የበለስ ዛፍ ቢቀርብ፡ ከቅጠል በቀር ምንም ፍሬ ሳያገኝባት በመቅረቱ፡ የተናገረው ቃል፡ እዚህ ላይ፡ ሊዘከር ይገባዋል።

ይኸውም፡ "ወይቤላ፡ 'ኢይኩን እንከ፡ ፍሬ እምውስቴትኪ ለዓለም!' ወየብሰት በጊዜሃ፡ ይእቲ በለስ።"

ማለትም፡ "'እንግዴህ ወዲህ፡ ለዘለዓለሙ፡ ፍሬ አይገኝብሽ!' አላት፤ በለሲቱም፡ ወዲያው ደረቀች።" የሚለው ነው። (ማቴ. ፳፩፥ ፲፰-፳።)

ታዲያ! እንዲህ በተባለችው፡ በዛሬዪቱ የአይሁድ እስራኤልና የወረራ ይዞታዋን፡ በብርቱ በሚቃወመው፡ በእስላሙ ዓለም በሚደገፉት ፍልስጥኤማውያን መካከል፡ ሲካኼድ የቆየው የተካረረ ግጭት፡ ጽዋው ሞልቶ ከሚገነፍልበት ደረጃ መቃረቡ፡ እነሆ፡ ከሶርያና ከፋርስ አግጣጫ ከሚወነጨፈው፡ ተጨማሪ ተፃራሪ ጠንቅ፡ በገሃድ መታየቱን ስለቀጠለ፡ የኹኔታውን አስከፊነትና አደገኛነት በቀላሉ ለመረዳት ያዳግታልን? አያዳግትም።

በሌላው ወገን ደግሞ፡ እየራሳቸውን፡ በይፋ፡ "ክርስቲያን ነን!" የሚሉት የዓለም መንግሥታት፡ "ኦርቶዶክስ፥ ካቶሊክና ወንጌላውያን" በተባሉት፡ አብያተ ክርስቲያኖቻቸው መሪነትና ግብረ አበርነት፡ ከአይሁዱ እስራኤል ጋር በመመሣጠር፡ የእግዚአብሔር መንግሥት በኾነችው ኢትዮጵያ ላይ፡ በእውቀታቸውና በገንዘባቸው፥ በሰብአዊ ብልሃታቸውና በጦር ኃይላቸው ተመክተው ለሚፈጽሙት፡ እጅግ የበዛና የተራቀቀ የደባ ተንኰላቸው፡ መለኮታዊው የፍርድ ዳኝነት፡ የትምክህታቸውን፡ የረዥም ዘመን ከንቱ ሕንፃ፡ እንዴት አድርጎ እንዳፈራረሰባቸውና እያፈራረሰባቸው እንዳለ፡ በገሃድ የሚታይ እውነታ ኾኖ፡ መገለጽ ከጀመረ፡ ውሎ አድሩዋል።

በየራሳቸው ሰብአዊ መንግሥትነት እንጂ፡ በእግዚአብሔር መንግሥትነት ፈጽመው የማያምኑትና በክርስትና ግብዝነታቸው ጨርሰው የማያፍሩት፡ እነዚሁ፡ የዓለም መንግሥታት፡ ከዚህ፡ የኃጢአት ግብራቸው የተነሣ፡ ከነአብያተ ክርስቲያኖቻቸው፡ ከእስላሙ ወገን፡ እየወረደባቸው ያለው የተግሣፅ ማስጠንቀቂያና መቅሠፍታዊ ቅጣት ሳያንሳቸው፡ በተደራራቢ እየወደቀባቸው ያለውን የችግር ቀንበር፡ ከየመነሻ ምክንያቱ ጋር፡ እዚህ ላይ፡ በየዓይነቱ እያወሱ ማቅረቡ ባላዳገተ ነበር፤ ነገር ግን፡ ዝርዝሩ ሰፊና ረጅም ስለኾነ፡ ለአኹኑ፡ ከእነዚህ መካከል፡ አንዱን ብቻ፡ ለአብነት ያህል መጥቀሱ እንደሚበቃ በማመን፡ ይህንኑ፡ እንደሚከተለው ገልጸነዋል፡-

ይህም፡ ቸሩ አምላክ፡ በፍጡራን የክፋት ኃይላት የማሰነችውን (የተበላሸችውን) ይህችን ዓለም ለማዳን ሲል፡ ዳግማዊት ሔዋን የኾነችው፡ ቅድስት እናቱ፡ ድንግል ማርያም፡ ቀደም ብላ ተወልዳባት፥ ከዚያም፡ ራሱ፡ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከእርሷ ተወልዶባት፡ ፍጥረተ ዓለሙ፡ በመጨረሻ፡ በኪዳነ ምሕረት፡ የታደሰባትን፡ የመስከረም ፩ ቀንን ዓውደ ዓመታዊ በዓል ዕለት፡ ክርስቲያኑ ዓለም፡ <u>አላገባብ፥ በሓሰት፡</u> ወደታኅሣሥ መጨረሻ ወዳሉት ቀኖች በመውሰዱ፡ እየከፈለ ያለውን ፍዳ የሚመለከተው  ነው።

አዎን! ይህች መስከረም ፩ ቀን፡ እግዚአብሔር አምላክ፡  ጥንት፡ ግዙፉን ዓለም፡ በመለኮታዊ ጥበቡ፡ ካለመኖር ወደመኖር ያመጣባት፥ ደግሞም፡ ይህንኑ ዓለም፡ በመልካም ይኖሩበት ዘንድ፡ የሰው ልጆች ወላጆች የኾኑትን፡ አዳምንና ሔዋንን የፈጠረባት ናት። አዎን! ይህች መስከረም ፩ ቀን፡ እግዚአብሔር አምላክ፡  በጠቅላላ፡ ፍጡራኑ ኹሉ፡ በያሉበትና ተሰባስበውም፡ የሥነ ፍጥረት ውበትና ድምቀት በሚሰፍንበት፡ በበጋው፡ የፀሓያማና የነፋሻ ወራት፡ በዚያ ኹሉ የፈጣሪ ቸርነት፡ ፍጹም ደስ ብሏቸው፡ የሓሤት በዓላቸውን እንዲያከብሩባት የመደበለት ዕለት ናት። አዎን! ይህ እግዚአብሔራዊ እውነታ፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ዘንድ፡ በሃይማኖት ታውቆና ተረጋግጦ፡ ይህች መስከረም ፩ ቀን፡ በዚህ እውነተኛ ምንነቷና ማንነቷ፡ በምግባራዊው ሥርዓት ስትከበር ኖራለች፤ አኹንም፡ እየኖረች ትገኛለች።

ዳሩ ግን፡ ክርስቲያኑ ዓለም፡ ይህን፡ የእግዚአብሔርን አማናዊ ሥርዓት በመሻር፡ እውነተኛው፡ የጌታችንና የእመቤታችን የልደት ቀንና እና የአዲስ ዓመት መግቢያ ዕለት፡ መስከረም ፩ ቀን መኾኑ ቀርቶ፡ የክረምቱ የበረዶ መዓት ወደሚወርድባቸውና ቀድሞ፡ የጣዖት አምልኮ ይፈጸምባቸው ወደነበሩት፡ ወደተለያዩት የታኅሣሥ ወር መጨረሻ ቀናት እንዲዛወር በማድረጉ፡ በየዓመቱ፥ በዚህ ወርና ሰሞን፡ በሚያከብራቸው፡ የገና እና የአዲሱ ዓመት በዓላት ጊዜ፡ እየደረሰበት ያለውን ሥቃይ፡ ፍጥረተ ዓለሙ፡ በግልጽ የሚያውቀው ስለኾነ፡ መዘርዘሩ አስፈላጊ አይኾንም። ክርስቲያኑ ግለሰብ፡ እነዚህን በዓላት፡ በቤቱና በሚወድዳቸው ቤተሰቡ፥ በዘመድ ወዳጆቹና በሚፈልጋቸው ቦታዎች እየተገኘ፡ በደስታና በዕረፍት ለማሳለፍና ለማክበር ሲል፡ በሚያደርገው ጉዞው ላይ፡ የሚደርስበትን አሠቃቂ ኹኔታ፥ በተለይ፡ ባለፉት ዓመታት የታየውን የበረዶ ውርጅብኝ መመልከቱ ይበቃል።

በእልፍ አእላፋት የሚቆጠረው፡ ክርስቲያኑ የዓለም ሕዝብ፡ በዚህ የአምልኮ ጠንቅ ምክንያት፡ ከሚወርድበት መቅሠፍት የተነሣ፡ እንኳንስ አድካሚና አሠቃቂ ጉዞውን ፈጽሞ፡ በተመኘው በአቱ (ቦታው)፡ በደኅና ደርሶ፡ የገናና የአዲስ ዓመት በዓሉን በመልካም ሊያከብር ይቅርና፡ በተጓጐለውና በተቋረጠው መንገዱ ላይ እንኳ፡ ተገቢውን መቆያ ለማግኘት ሳይቻለው ቀርቶ፡ ከጉዞውም፣ ከበዓሉም ሳይኾን፡ ጊዜውን፡ በየአየር ማረፊያው መናኸሪያ አዳራሽ ተቀራምዶ ማሳለፍ ግድ ኾኖበታል።

ይህን ኹሉ ችግር ያመጣው፡ ራሱ ሰው፡ በገዛ እጁ በፈጸመው ስሕተት መኾኑን፡ ራሱም ስለሚያውቀው፡ ራሱን በንስሓ፥ ተገቢውን የእግዚአብሔርንም ሥርዓት፡ ወደመደበኛ ቀኑ መልሶ በማስተካከል፡ በዚህ ኃጢአት ምክንያት፡ በየዓመቱ ከሚደርስበት ጠንቀኛ ችግር ራሱን ማዳን ይኖርበታል።

እንግዴህ፡ የብዙዎች መሥዋዕትነት የተከፈለበት፡ ይህ ኹሉ የማስጠንቀቂያ ደወል ያለማቋረጥ እየተሰማ በሚገኝበት፡ በአኹኑ ጊዜ፡ ራሱን፡ "ኢትዮጵያዊ ነኝ" የሚለው፡ ይህ ትውልድ፡ ከክህደቱ፥ ከዓመፀኝነቱና ከአመንዝሪነቱ ኃጢአት፡ በልበ ደንዳናነት፡ ወደንስሓ፡ "አልመለስ!" ብሎ፡ በቤተ ሕዝቡና በቤተ ምልክናው ብቻ ሳይኾን፡ በይበልጥ፡ በቤተ ክህነቱ በኩል እያካኼደ ያለውን አሳፋሪ ድርጊት፡ በበለጠ እያባባሰው፡ ሲቀጥልበት መታየቱ እጅግ ያስገርማል! ከዚህ ይልቅ፡ አኹንም ቢኾን፡ ይህ ኹሉ ኃይለኛ ክሥተት፡ "ምንን የሚያመለክት ይኾን?" ብሎ ማጤን፡ የሚያስፈልገው ይኾናል።

## ጾም፥ ጸሎት፥ ምጽዋትና ንስሓ፡ ምንድር ናቸው?

እስከዚህ ድረስ፡ ስለዚችው፡ ስለኢትዮጵያ ጾም ስንነጋገር፡ "'ጾም፥ ጸሎት፥ ምጽዋትና ንስሓ፡ ምንድር ናቸው? ለምንስ ያስፈልጉናል?" የሚሉ ይኖሩ ይኾናል፤ ለዚህ ጥያቄ፡ መልስ የሚኾነውን ቃል፡ ባጭር እንግለጽላችሁ!

እንደምታውቁትና በእየራሳችሁ እንደሚሰማችሁ፡ ኢትዮጵያዊው፡ ከራሱ ተፈጥሮና አካል ጀምሮ፡ እምነቱና ምግባሩ፥ አስተሳሰቡና አኗኗሩ፥ በጠቅላላ ህልውናውና ሕይወቱ፡ የእግዚአብሔርና በእግዚአብሔር፥ ከእግዚአብሔርና ለእግዚአብሔር ነው:: ይህንም እውነታ፡ በሥነ ፍጥረትና በሥነ መለኮት ምሥጢራት ላይ ተመሥርቶና ታንጾ፥ ከእነዚህም ሠርፆና በእነዚህ ቆሞ፡ በሕያውነት የሚኖርበት ኹለንተናው ያረጋግጣል::

"ጾም"፡ አንድ ሰብአዊ ፍጡር፡ ራሱን ተቆጣጥሮ፡ ሥጋዊ ፍላጎቱን በመግታት፡ ወደልቡናው ተመልሶ፡ አፍአዊና ውሳጣዊ ኹለንተናውን ለመመርመርና ከክፉ አስተሳሰብ ለማጽዳት መቻል ነው:: በተለይ፡ ለኢትዮጵያዊው ግን፡ ከእግዚአብሔር ጋር ለተዋሐደው፡ ኢትዮጵያዊ ምግባሩ፡ መታወቂያ ምልክቱ ነው::

"ጸሎት"፡ ያው ሰብአዊ ፍጡር፡ በሃይማኖት አምልኮና በእውነት መንፈስ ኾኖ፡ በመልኩ ከፈጠረው፡ ከእግዚአብሔር ጋር፡ ብቻ ለብቻ፥ በመሰሎች፡ ፍጹም አንድነትም፡ አብሮ መነጋገር ነው::

"ምጽዋት"፡ ያው ሰብአዊ ፍጡር፡ ሌላውን ፍጡር፥ ሰብአዊ ወገኑን ጭምር፡ በባልንጀርነት ፍቅር አይቶና ተቀብሎ፡ ለዚያ ፍጡር፡ በአሳብ፥ በንግግርና በግብር፡ በጎ ነገርን ማድረግ ነው::

በ"ጾም" ፋንታ፡ "የረኃብ ዓድማ" የሚባለውን የመሰሉትን ይትበሃሎች ለመተካት የሚደረገውን ሙከራ፡ ማጤን አግባብ ይኾናል።

የሰዎችና በሰዎች፥ ወደሰዎችም የሚያመራው፡ “የረኃብ ዓድማ” ዘዬ፡ በእግዚአብሔር ለማያምኑ፡ ለአሕዛብና ለአረማውያን ወገኖች፡ መለያቸው እንዲኾን፡ ራሳቸው የመረጡት አገላለጽ ሊኾን ይችላል፤ ውጤቱም፡ በድንጋይ ላይ እንደፈሰሰ ውኃ፡ ተንኖ መቅረት፥ ማለትም፡ ፍጻሜው፡ ሞት ነው፡፡ “ጾም” ግን፡ የእግዚአብሔርና በእግዚአብሔር፥ ከእግዚአብሔርና ለእግዚአብሔርም ኾኖ፥ ወደእግዚአብሔር ያደርሳል፤ ውጤቱም፡ በወንዝ ዳር እንደበቀለች ተክል፡ ለምልሞ፡ መልካሙን ፍሬ ማፍራት፥ ማለትም፡ ፍጻሜው ሕይወት ነው፡፡

ወገኖቻችን! እስኪ፡ ላንዲት አፍታ፡ ቆም ብላችሁ፡ ከ፲፱፻፷፯ ዓ. ም. በፊትና ከዚያ በኋላ፥ እስካኹን፡ የኾነውንና አኹን፡ በዚህ ትውልድ ላይ እየደረሰ ያለውን ኹሉ፡ በዓይነ ሕሊናችሁ ተመልከቱት! ለመኾኑ፡ ይህን ትውልድ፡ ለዚህ ኹሉ ችግርና ውድቀት የዳረገው፡ ምን ይመስላችኋል? ተራና ጥቃቅን መስለው ከሚታዩን፡ ከእኒህ ዓይነቶቹ ስሕተቶች፡ ባለመጠንቀቁና ነቅቶ ባለመጠበቁ፥ ከዚህ የተነሣም፡ እያንዳንዱ፡ የትውልዱ አባል፡ የኃላፊነት ግዳጁን ባለመፈጸሙ አይደለምን? ነው እኮ!

ታዲያ! ይኸው ትውልድ፡ ይህንኑ አውቆ፡ በዚህ ረገድ፡ ማስተዋልና ማመዛዘን፥ የሚጠበቅበትንም ድርሻ፡ በያለበት መፈጸም የሚጀምረው፡ መቼ ነው? የእስካኹኑና አኹን እያሠቃየው ያለው መከራ አይበቃውምን? ይህ ትውልድ፡ ከቶ፡ ምን ነካው? የተደረገበት አዚም፥ አፍዝ አደንግዝስ አለን? ምን እስኪኾን ነው የሚጠብቀው!? የሚሰማ ጆሮ ካለው፡ “እንግዴህማ፡ ንቃ እንጂ!” የሚለውን፡ የኢትዮጵያን የማንቂያ ደወል፡ በዚህ አጋጣሚ እያሰማነው፡ ወደሚቀጥለው ርእስ እንኼዳለን፡፡

በመጨረሻ፡ “ንስሓ”፡ ሕሊናችን የሚያውቀውንና የሚነግረንን፡ በአሳብ፥ በቃልና በድርጊት የፈጸምነውን ጥፋት፥ በደልና ክፋት አምኖ፡ ራስንና እግዚአብሔርን፡ ከልብ ይቅርታ መጠየቅ ነው፡፡ ራስንና እግዚአብሔርን ይቅርታ የመጠየቁ ግዳጅ፡ በመንፈስ ብቻ የሚፈጸም ስለኾነ፡ በዚህ ረገድ ችግር አይኖርም፤ የበደለን ሰው፡ ይቅር ለማለት ኾነ፡ የበደልነውን ሰው፡ ይቅርታ ለመጠየቅ ግን፡ በአካል መገኘት ያስፈልገን ይኾናል፡፡ በዚህ በኩል ደግሞ፡ ይቅር የማለቱን ኾነ፡ ይቅርታ የመጠየቁን ግዳጅ፡ ከቻልን፡ በግንባር፥ ካልቻልንም፡ በያለንበት ኾነን፡ በመንፈስና በእውነት መፈጸም ስለምንችል፡ በዚህ በኩል ላለው፡ በንስሓችን አፈጻጸምም ረገድ፡ ችግር እንደማይኖር፡ ሊታወቅ ያስፈልጋል፡፡

እዚህ ላይ፡ ልናስታውስ የሚገባን፡ አንድ ቍም ነገር አለ፤ ይህም፡ "ንስሓ" ማለት፡ በዚህ ይዘትና መልክ፡ ካሉበት፡ ከሥጋዊው የሓሰት አስተሳሰብና ክፉ ድርጊት፡ ወደመንፈሳዊው እውነተኛ እምነትና መልካም ምግባር መመለስ ማለት ነው። ይህንም፡ በአጭር ምሳሌ ማስረዳት ይቻላል፤ ይኸውም፡ በጎጂ መጠጥና የዕፅዋት ጢስ፡ ጤንነቱን ያጣ፡ አንድ ሰው፡ ወደሓኪም ኼዶ የታዘዘለትን መድኃኒት መውሰድና በዚያ መጠቀም ብቻ፡ ከበሽታው ሊያድነው አይችልም።

ለበሽታው፡ መነሻና መጠናከር ምክንያት የኾነውን ጠንቅ፡ በቅድሚያ፡ ጨርሶ፡ ከራሱ ማስወገድና ራሱን ከዚያ ጠንቅ፡ ማለትም፡ ያን መጠጥ ከመጠጣትና ዕፅዋቱን ከማጤስ መለየት አለበት።

አለዚያ፡ ለጤንነቱ መናጋት መነሻና ምክንያት የኾነው፡ ያ ጠንቅ፡ እንዳለ ኾኖ እየቀጠለ እስካለ ድረስ፡ ያ ሕመምተኛ፡ የታዘዘለትን የሕክምና መድኃኒት፡ በትክክልና በጊዜው እየወሰደ ቢኾንም እንኳ፡ በሽታው እየባሰበት ከመኼድ በቀር ሊድን፡ ከቶ አይቻለውም።

እንደዚሁ ኹሉ፡ አንድ ሰው፥ ወይም ትውልድ፡ በኃጢአቱ፡ ማለትም፡ በራሱ ጥፋት፥ ወይም፡ በተሳሳተ አስተሳሰቡና በክፋት ዝንባሌው እያካኼደውና እየፈጸመው ካለው ሥራ የተነሣ፡ ከሚደርስበት ችግርና መከራ መዳን የሚችለው፡ በቅድሚያ፡ የሚገኝበትን፡ ያን ኹኔታና ድርጊት "ትክክል አይደለም!" ብሎ፡ ተጸጽቶበት፡ ጨርሶ ሲተወውና ከዚያ፡ ራሱን አጽድቶ ሲለይ ብቻ ነው። አለዚያ፡ በዚያ የተሳሳተ አስተሳሰቡና የክፋት ሥራው እንደቀጠለበት እያለ፡ "ንስሓ ገብቻለሁ!" ብሎ፡ ሥጋ ወደሙ ቢቀበል፥ በጸሎት ቢጠመድና የተለያየ አያሌ የበጎ አድራጎት ምግባራትንም ቢፈጽም እንኳ፡ ሥቃዩ እየከበደበትና እየጸናበት ከመኼድ በቀር፡ ከሚገኝበት ችግርና መከራ ሊላለቀቅ ከቶ አይቻለውም።

በዚህ ትውልድ ላይ እየደረሰ የሚታየው፡ እጅግ መራራና ፍሬ አልባ ውጤት፡ በትክክል፡ ይህን የመሰለ ኾኖ ሊገኝ የቻለው፡ በዚህ ምክንያት መኾኑ፡ ሊታወቅ ይገባል።

እንዲህ አድርገን፡ እየራሳችንን፡ ከራሳችን፥ ከእግዚአብሔርና ከባልንጀራችን ጋር በእግዚአብሔርዋ እውነት ካስታረቅን፥ ካስተካከልንም፡ በውስጣችንና በውጫችን፡ ሰላምና ፍቅር ይሰፍናሉ፤ ሰውነታችንም፡ ለእግዚአብሔር ማደሪያነት የበቃ ይኾናል።

በዚህ ጊዜ ነው፡ እያንዳንዳችን፡ ቅዱስ ቁርባንን፡ በመቀበል፡ ጾማችንን፡ በእውነትና በትክክል መፈጸማችንን፡ ለራሳችን፥ ለእግዚአብሔርና ለባልንጀራችን የምናረጋግጠው:: የድኅነታችን (የመዳናችን) ማኅተም፡ የክርስቶስ፡ ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም ነውና:: ያለዚያ፡ ድካማችን ኹሉ፡ ከንቱ ይኾናል:: ስለዚህ፡ ይህችን፡ የሦስት ቀናት ጾመ ኢትዮጵያችንን፡ በትክክል ልንፈጽማት ይቻለን ዘንድ፡ ከአኹኗ አፍታ ጀምረን፡ ተገቢውን፡ የመንፈስ፥ የአእምሮና የአካል ትጥቅ ዝግጅታችንን ማከናወን ይገባናል::

ይህንም የምናደርገው፡ ሙሴ፡ በእግዚአብሔር አዛዥነትና አበጋዝነት፡ የእሥራኤልን ሕዝብ፡ ከግብፅ የባርነት ቀንበር፡ ነጻ ካወጣቸው በኋላ፡ እየመራ፡ ለመጨረሻው ድል፡ በኤርትራ ባሕር ዳር ቆመው በነበረበት ኹኔታቸው ዓይነት፡ ማለት ነው::

ዛሬም፡ እኛ፡ የኢትዮጵያ ልጆች፡ በኢየሱስ ክርስቶስና በድንግል ማርያም መሪነት፡ ከዲያብሎስ ኃይላት አንጻር፡ በምናካኺደው፡ በዚህ፡ በ"ጾመ ኢትዮጵያ" የገድል ሰልፋችን ጊዜ፡ እየራሳችንን፡ ለመጨረሻው ድል ለማብቃት፡ እንዲህ፡ የተዘጋጀን ኾነን መገኘት ያስፈልገናል::

እኒህ፡ ሦስት ቀናት፡ ለአርባ ዓመታት ያህል ለኾነ ዘመን፡ ያለማቋረጥ፡ እንደጎርፍ የፈሰሰውን፡ የኢትዮጵያን፡ የወንዶችና የሴቶች ልጆቿን፥ የሕፃናቷንና የወጣቶቿን፥ የጎልማሶቿንና የአዋቂዎቿን፥ የአዛውንቷንና የአረጋውያኗን ደምና እንባ፡ "በቃ!" ብሎ፡ የቃል ኪዳን አምላካችን እግዚአብሔር፡ ይቅርታውን እንዲለግሠን፡ የመጨረሻ ልመናችንን የምናቀርብባቸው ናቸው።

አዎን! እኒሁ ሕዝቧ፡ በተከታታይ እየወረደባቸው ያለውን፡ ረኃብና ጥማት፥ እርዛትና እንግልት፥ ሕመምና ሥቃይ፥ ግፍና እሥራት፥ የመጠጊያ እጦትና ስደት፥ ግድያና የእርስ በርስ ዕልቂት፡ ቸሩ ፈጣሪያችን፡ ስለኃጢኣታችን ስርየት፡ ለአቤቱታና ለንስሓ እንደቀረበ መሥዋዕት አድርጎ እንዲቀበልልን የምንማጸንባቸው ናቸው።

ይህ ትውልድ፡ የፈጣሪውን ይቅርታና የአምላኩን ምሕረት ለማግኘት ደግሞ፡ ከእርሱ፡ ከፈጣሪውና ከአምላኩ ተለይቶ፥ ቃል ኪዳኑንም አፍርሶ፡ የባዕዳኑን ሥርዓት በመከተል ከቆየበት፡ የስሕተት አካኼዱ፡ በእውነተኛ ንስሓ ተመልሶ፡ ሃይማኖታዊ አምልኮውን፡ በቅድሚያ ሊያስተካክል ያስፈልገዋል። ይህችን፡ የሦስት ቀናት ጾም፡ እንዲህ፡ እንደነነዌ ሕዝብ፡ እግዚአብሔር፡ በሚቀበለው መንፈስ ከፈጸምናት፡ ለአርባ ዓመታት ያህል ለኾነ ዘመን፡ ሳያባራ የቀጠለውን፡ የፈተና እሳትና የመከራ ማዕበል፡ ይህ ትውልድ፡ ከራሱ ላይ፡ ጨርሶ ማስወገድ እንደሚችል፡ መለኮታዊው የምሕረት ቃል ኪዳን አረጋግጦለታል፤ እኛማ፡ በምንም፡ የምንጠራጠረው አይደለም።

## የፈተናው እሳትና የመከራው ማዕበል፡ ለምን ቀጠለ?

እንዲህ ከኾነ፡ ታዲያ! የፈተናው እሳትና የመከራው ማዕበል፡ በዚህ ትውልድ ላይ፡ በተለየ መልኩ፡ እየተራቀቀና እየተጠናከረ፥ እየተስፋፋም ከመቀጠል በቀር፡ ለምን የመሻሻልና የመርገብ ምልክትን አላሳየም? የዚህ ጥያቄ መልስ፡ ግልጽና ቅርብ ነው።

የእግዚአብሔርን ነገር፡ በየልቦናችን የሚያስገነዝበን ኢትዮጵያዊነታችን እኮ፡ የዚህን ምክንያት፡ ዘወትር፡ ለየራሳችን መንገሩን አላቋረጠም፤ ነገር ግን፡ ይህ፡ የኢትዮጵያ ትውልድ፡ ፈጣሪው እግዚአብሔር፡ በዚህ ኢትዮጵያዊነቱ አማካይነት፡ በየልቦናው አኑሮ ያስተማረውንና በየጊዜው የሚነግረውን ኹሉ፡ "እምቢ! አልሰማም!" አለ፤ የሚያዳምጠውና የሚከተለው፥ የሚፈራውም፡ ሰዎች፥ ያውም ባዕዳን ተፃራሪዎቹ የሚሉትንና ያስተማሩትን ብቻ ኾነ! ከዚህ የተነሣ፡ እየባሰ የኼደው፡ የፈተናው እሳትና የመከራው ማዕበል፡ በበለጠ እያጥለቀለቀውና እያሰጠመው ኼዶ፡ ይኸው፡ ዛሬ፡ ከመጨረሻው የጥፋት ፍጻሜ ደርሶ፡ ራሱን አግኝቶታል።

አዎን! ይህ ኹሉ መዓት፡ በትውልዱ ላይ የወረደበት፥ እየጸናበት የቀጠለውም፡ እግዚአብሔርንና ቃል ኪዳኑን፡ በክህደት፥ በዓመፅና በአመንዝራነት በመተዉ ነው፤ ይህን እውነታ፡ ይኸው ኢትዮጵያዊነቱ፡ እንደእስከዛሬው ኹሉ፡ አኹንም፡ እነሆ እያስገነዘበው ይገኛል።

ይኸው መከራ እንዲወገድለትም፡ በፈጣሪውና በቃል ኪዳኑ ላይ የፈጸመውን፡ ይህንኑ ኃጢኣቱን፡ በንስሓ በማጽዳት፡ ክህደቱን፡ በሃይማኖት፥ ዓመፁን፡ በበጎ ምግባር፥ አመንዝራነቱንም፡ በታማኝነት ተክቶና አድሶ፡ ከአምላኩ ጋር ዕርቅ እንዲያደርግ፡ ይማፀነዋል፡፡

በአኹኑ ጊዜ፡ ይህ መልእክት፡ ለዚህ ኢትዮጵያዊ ትውልድ አባል ኹሉ፡ እንዲደርስ በማሰብ የተላለፈበት፥ "ተፈጻሚነትም ይኖረዋል!" ተብሎ የሚታመንበት፡ በቂ ምክንያት አለ፤ ይህም፡ ለአርባ ዓመታት ያህል ለኾነ ዘመን የደረሰው፡ ሥፍር ቍጥር የሌለው መከራና ሥቃይ፡ የእያንዳንዱን ኢትዮጵያዊ ልቦና፡ እንደነነዌ ሰዎች፡ ወደእውነተኛው የጸጸት መንፈስ ሊመልሰው እንደቻለ ስለተገመተ ነው፡፡ "ለንስሓ መብቃት"፡ ይህ ነውና፡፡

የእግዚአብሔር ምሕረት እኮ፡ ያለማቋረጥ እንደምንተነፍሰው ንጹሕ አየር፥ እንደምንመላለስበት የፀሓይ ብርሃን፥ እንደምንጠጣው ጥሩ ውኃና እንደቆምንባት ፍሬያማ ምድር፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነት፡ በተለይ፡ ከዛሬ ኹለት ሺህ ስድስት ዓመታት ጀምሮ፡ ይኸው፡ ከእያንዳንዳችንና ከኹላችን ጋር፡ ያለማቋረጥ፡ አብሮን ይኖራል።

እውነተኛው ፍላጎት ካለንም፡ ይህን፡ የእግዚአብሔርን ምሕረት፡ በቅጽበት ልናገኘው እኮ እንችላለን፡፡ ነገር ግን፡ ይህንኑ፡ የእግዚአብሔርን ምሕረት፡ ይኸው ኢትዮጵያዊ ትውልድ፡ በየራሱ ውሳኔ፡ "የለም!" ብሎ፡ እንደሌለ ቆጠረው፤ "አልፈልገውም!" ብሎም፡ ከየራሱ አራቀው፤ ስለዚህ፡ አኹን፡ በዕድሜያችን፡ እነሆ፡ ለአርባ ዓመታት ያህል ለኾነ ዘመን፡ እየቀጠለ በኼደው፡ በዚህ፡ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት፥ ሥቃይና ጭንቀት ብቻ ሳይኾን፡ ደም መፋሰስ ጭምር በበዛበትና በጸናበት ህልውና ውስጥ፡ ይህ ትውልድ እንዲማቅቅ ተገድዶ፡ እነሆ፡ በኃጢኣት ጨለማ ተውጦ ሲዳክርና በድካም ሲባዝን ይገኛል፡፡

የቃል ኪዳን አምላካችን እግዚአብሔር፡ "**ወለክሙሰ፡ ሥዕርተ ርእስክሙኒ ኵሉ፡ ኍሉቅ ውእቱ።**" ማለትም፡ "**የእናንተስ፡ የራስ ጸጕራችሁ ኹሉ እንኳ፡ በእኔ ዘንድ የተቈጠረ ነው።**" ብሎ በተናገረው ቃሉ መሠረት፡ የራስ ጸጉራችንን ሳይቀር ይጠብቃል፤ ይንከባከባልም፤ እንዲያውም፡ እኛን ሰዎችን፡ ከሰይጣን፥ ከኃጢኣትና ከሞት ለማዳን፡ ራሱን ቤዛ አድርጎ ሠውቶልናል፤ አንድ ፍጡሩ፡ መገደል ቀርቶ፡ አነስተኛ ጉዳትም እንኳ እንዲደርስበት አይፈልግም፡፡ ለእኛ፡ ለቃል ኪዳን አማኞቹና ተከታዮቹም፡ "**ጠላቶቻችሁን ውደዱ! በክፉ ሥራቸው ፈንታ፡ በጎ አድርጉላቸው! የበደሏችሁንም ኹሉ ይቅር በሉ!**" የሚል፡ የደግነት መመሪያን ሰጠ እንጂ፡ እንኳንስ እንድንበቀላቸው ይቅርና፡ ከዚያ በኋላ፡ እንድንቀየማቸው እንኳ፡ አልፈቀደልንም፡፡ (ማቴ. ፭፥ ፵፬። ፲፥ ፴።)

ሰዎች፡ በልዩ ልዩ መንገድ፡ በእየራሳቸው ላይ ጉዳትንና ሥቃይን እንዲያመጡ፥ እርስ በርሳቸውም ተጣላልተው እንዲጋደሉ ማድረግ የሚያስደስተው፥ ደማቸውንም አስፈስሶ፡ ያን መጠጣት የሚወድደው፡ ዲያብሎስ ነው፤ በኢትዮጵያና በልጆቿ ተቃዋሚዎችም ላይ አድሮ፡ ይህንና ሌላውን ኹሉ፡ የክፋትና የጥፋት ድርጊትን የሚያስፈጽመው፡ እርሱ መኾኑን የማያውቅ ኢትዮጵያዊ ይኖራል ብሎ መገመቱ ያዳግታል፡፡

በኢትዮጵያ ምድር ላይ፡ ቀድሞ፡ በኅቡዕ (በሥውር) ሲሠራ ከቆየ በኋላ፡ ከ፲፱፻፷፯ ዓ. ም. ጀምሮ ግን፡ ከነሠራዊቱ፡ በይፋ ነግሦ እንደሚገዛ፡ እነሆ፡ ለመላው ዓለም፡ ገሃድ በኾነው፡ የግፍና የጭካኔ ድርጊቱ፡ ተረጋግጦ ተመስክሩዋል፤ ይኸውም፡ ቊጥሩ፡ በእልፍ አእላፋት በሚታሰብ መጠን፡ ወንድማማችና እኅትማማች የኾኑት ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ በእርስ በርስና በድንበር ጦርነት፡ ደም በመፋሰስ የተላለቁበት፥ አኹንም እየቀጠለ እንዲኼድ የተደረገበት ታላቁ ደባ ነው:: ለዚህም፡ ለአርባ ዓመታት ያህል ለኾነ ዘመን፡ ባዕዳንና የኢትዮጵያ ተጻራሪዎች፡ በሚለግሡት ብቻ ሳይኾን፡ ከደኃው የኢትዮጵያ ሕዝብ በተሰበሰበው የግብር ገንዘብ፡ ከእነርሱ እየተሸመተ ያለው፡ የጦር መሣሪያ ብዛት፡ በቂ ማስረጃ ይኾናል::

## እግዚአብሔራዊው ሥርዓትና ሰብአውያኑ ፍልስፍናዎች።

ታዲያ! በተንኰሉ፥ በገንዘቡና በጦር ኃይሉ ይዞታ ረገድ፡ እንዲህ ተሟልቶ የተሰናዳውንና የተቀናበረውን፡ ይህን፡ የዲያብሎስንና የኢትዮጵያን ጠላቶች የማጥቂያ ዝግጅትና ድርጅት፡ ተቋቁሞ ለማስወገድ የሚቻለው፡ ሌላ ተወዳዳሪ ኃይል፡ ከእግዚአብሔር በቀር፡ ከቶ ማን ሊኖር ይችላል? አዎን! ማንም የለም፤ ስለዚህ ነው፡ ይህ "ጾመ ኢትዮጵያ" ያስፈለገው::

ወገኖቻችን ሆይ! እግዚአብሔር፡ እንደሰው አይደለም:: እንኳንስ፡ በቅድስት እናቱ ድንግል ማርያም ምክንያት፡ ከእርሱ ጋር የቃል ኪዳን መተሣሠር ያለን፡ እኛን፡ የኢትዮጵያን ልጆች እንቅርና፡ ሌላውን፡ ማንኛውንም፡ የተማመነበትንና በእውነት የሚጠራውን ፍጡሩንም እንኳን ቢኾን፡ አያሳፍርም፤ አሳፍሮም አያውቅም፤ እርሱ፡ በኪዳኑ፡ ፍጹም የታመነ ነው፤ በቃሉም፡ የጸና ነው፤ የቃል ኪዳን ተዋዋዩ የኾነ ፍጡሩ፡ ቃሉን አፍርሶ፡ ይክደዋል እንጂ፡ እርሱ፡ ፈጣሪ፡ በምንም መልክ፡ ከታማኝነቱ፡ አይነዋወጽም::

የሰዎች ቃል ኪዳንማ፡ ጉዱ፡ እንደገና ወጥቶና ተጋልጦ፡ ይኸው፡ ዕርቃኑን ታየ አይደለምን? የዛሬው የኢትዮጵያ ትውልድ፡ የባዕዳንን ሰዎች፡ Capitalism, Socialism, Communism እና Democracy ከተባሉት ፍልስፍናዎቻቸው ጋር፡ ፈልጓቸው፥ ፈቅዷቸውና አምኗቸው የተቀበላቸው መኾኑን፥ አብሮም፡ ሽር ጉድ ማለቱን መካድ፡ ከቶ ይቻላልን? አይቻልም፤ እያንዳንዱን ፍልስፍናስ፡ በተለያየ የአገዛዝ ፈሊጥ፡ በየተራ፡ በራሱና በአገሩ፥ በወገኑም ህልውና ላይ አስፍኖ፡ እንዲሠለጥን አላደረገምን? ስላደረገውማ፡ ይኸው፡ አኹን፡ ኹሉንም፡ በፍሬው፡ ራሱ፡ እያየው ነው! ያ ፍላጎቱ፥ ያ ፈቃዱና ያ እምነቱ ካስገኙለት መራራ ፍሬ፡ ባዕዳኑ፡ ጨምቀው የሞሉለትንም ጽዋ፡ ይኸው፡ ቋቅ እስኪለው ድረስ፡ ጨልጦ እንዲጠጣው እያስገደዱት ነው!

ከኹሉ ይልቅ፡ እጅግ የሚገርመውና የሚያስተክዘው፡ ይህ የኢትዮጵያ ትውልድ፡ ለእኒህ፡ ለእያንዳንዱ ፍልስፍናዎች፡ በየተራ፡ የወገኖቹን ሕይወት፡ በገፍ እያጠፋ፡ ሥጋቸውን፡ ጭዳ አድርጎ፡ ለዲያብሎስ መብል፥ ደማቸውንም፡ በግፍ እያፈሰሰ፡ ለዚሁ የክፋት ጣዖት፡ መጠጥ አድርጎ ማቅረቡ ነው:: በአገሩና በወገኑ፥ በማንነቱም ላይ፡ ይህን ኹሉ አሰቃቂ በደል ፈጽሞ፡ እስካኹን፡ የማፈርና የማዘን፥ የመጸጸትና ንስሓ የመግባት ዝንባሌን እንኳ፡ አለማሳየቱ፡ አዎን! በይበልጥ ያስገርማል፤ ያስተክዛልም።

እንዲህ፡ በክፋት የናወዘው፥ ግራ የገባውና መቅኖ ያጣው፡ ይህ፡ ኢትዮጵያዊ ትውልድ፡ በዚህ ድርጊቱ፡ የተረፈው ነገር ቢኖር፡ አንድ ብቻ ኾኖ ይታያል፤ ይኸውም፡ እርስ በርሱ የማይተማመን ከመኾኑ የተነሣ፡ በመሓላ የተገባባውን ቃሉን እያፈረሰና እየተካካደ፡ መለያየት፥ ባለፉት ያልተቋረጡ ዘመናትና በአኹኑ ጊዜም፡ ያንኑ፡ የባዕዳኑን ፈሊጥ ተከትሎ፡ በኢትዮጵያና በመላው ዓለም እየተሰለፈ፡ ወደእነዚሁ አጥቂዎቹ፡ ያለማቋረጥ የመጮህ ግዴታን፡ እንደቀንበር ተሸክሞ መዞሩ ነው:: ለዚያውም ቢኾን፡ ያ ኹሉ፡ በከፍተኛ ድምፅ፡ በያለበት፡ የተስተጋባው የኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያውያት ጩኸት፡ ሰሚና ተቀባይ ሳያገኝ፡ ከንቱ ኾኖ ለመቅረቱ፡ ከራሱ ምስክርነት ያለፈ፡ ሌላ ማስረጃ አያስፈልግም::

አዎን! ከጥንት ጀምሮ እስከዛሬ እንደታየው፥ ዛሬና ወደፊትም እንደሚታየው፡ ለፍጡሩ፥ በተለይም፡ ለኢትዮጵያውያንና ለኢትዮጵያውያት፡ የታመነ አምላካቸው፥ ወገናቸውና ወዳጃቸው፡ እግዚአብሔር ብቻ ነው:: ሰው፡ ባዕዱም ኾነ፥ የራሴ የሚሉት ወገን ጭምር፡ ፈጽሞ ሊታመን አይቻልም:: ይህን እውነታ፡ አረጋግጦ ለማስረዳት፡ እንግዴህ ወዲህ፡ ከዛሬው የኢትዮጵያ ትውልድ፡ የበለጠና የተሻለ ምስክር ይኖራል ብለን አናስብም::

ይህ ትውልድ፡ አባቶቻችንንና እናቶቻችንን፡ አልሰማቸውም፥ ሊሰማቸውም አልፈለገም እንጂ፡ እነርሱማ፡ እግዚአብሔርን ትቶ፡ በሰው የሚታመን ኹሉ፡ የተረገመ እንደኾነ እንደሚናገረው የመጽሓፍ ቃል፡ በሚቆጠረው ዘይቤያቸው፡ "ሰውን፡ ውደደው እንጂ፡ አትመነው!" ደግሞም፡ "ሰውን ማመን፡ ቀብሮ ነው!" ሲሉ፡ አስቀድመው፡ አስጠንቅቀውት ነበር::

ስለዚህ፡ እኛ፡ በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያ ልጆች፡ የግልም ኾነ፥ የጋራ ፍላጎታችን፡ በእርግጥ ይፈጸምልን ዘንድ፥ ጩኸታችንም፡ ተገቢውን ምላሽ ያስገኝልን ዘንድ፡ ምንጊዜም፡ ግንኙነታችንንና ንግግራችንን፥ ውለታችንንና ስምምነታችንን፡ ልናካኼድ፥ ልንፈጽምም የሚገባን፡ የቃል ኪዳን አምላካችን ከኾነው፡ ከእግዚአብሔር ጋር ብቻ ነው፤ ይህንም፡ **"ኢትዮጵያ፡ እጆቿን፡ ወደእግዚአብሔር ትዘረጋለች!"** በሚለው፡ የነቢያት ቃል፡ ከጥንት ከመሠረቱ፡ ከፈጣሪያችን የተቀበልነው ሥርዓታችን፡ አበክሮ ያስገነዝበናል::

ከዚህ የተነሣ፡ የምናምነው፡ እግዚአብሔርን፥ የምንታመነውም፡ በእግዚአብሔር ብቻ ሊኾን ይገባል፤ እርስ በርሳችን እንኳ፡ ልንተማመን የሚገባን፡ በእግዚአብሔር በኩል እንዲኾን፡ ግድ ይኾናል፤ አለዚያ፡ አንዳችን፡ የአንዳችንን ውስጣዊ ማንነት ስለማናውቅ፡ እርስ በእርሳችን እንኳ ለመተማመን እንዴት ይቻለናል? አይቻለንም::

በሰዎች መካከል ያለው ግንኙነት፥ በባልና ሚስት መካከል ያለው፡ የጋብቻ አንድነት ጭምር፡ በዚህ እውነታ ላይ የተመሠረተ ካልኾነ በቀር፡ ሊጸና  አይችልም፤ እስከመፍረስ የሚደርሰውም፡ በዚህ እውነታ ላይ ሳይመሠረት በመቅረቱ ምክንያት መኾኑንና ማወቁ፡ ለማንም ሰው ይጠቅመዋል፡፡

ኢትዮጵያዊዉን ሥርዓት፡ ለመግለጽ ሲባል፡ ይህ አስተያየት ቢሠነዘርም፡ Capitalism, Socialism, Communism እና  Democracy የሚባሉት፡ የባዕዳኑ ፍልስፍናዎች፡ "አይሠሩም፥ አይጠቅሙም" ማለት አይደለም። እነዚህ ፍልስፍናዎች፡ የሰዎች እንደመኾናቸው መጠን፡ ሰዎች፡ በፈለጉትና ለራሳቸው በሚጠቅሟቸው መንገድ፡ እንዲሠራባቸው የሚያደርጉበት፡ የተለያየ ሰውኛ ፈሊጥ አላቸው፡፡ ይህ ፈሊጥ፡ ሰውኛ ብቻ ሳይኾን፡ ሰይጣናዊ እስከመኾን ሊደርስ ስለሚችል፡ የእግዚአብሔር ከኾነው ሥርዓት ጋር ሊስማማ ቀርቶ፡ በሩቁ እንኳ ሊተያይ አይቻለውም፡፡ እስካኹን ደርሶ እንደታየው፡ ከሰብአዊነት ውጪ የኾኑ፡ የግፍ ድርጊቶች፡ በረቂቁም ኾነ፡ በግዙፉ መንገድ የሚካኼዱትና  የሚፈጸሙት፡ በእነዚህ ፍልስፍናዎች ስም ኾኖ ይገኛል፤ ይህም፡ የፈሊጡ ምንጮች፡ የተፈለሰፉትና በተግባር ላይ የዋሉት፥ ሊሰፍኑም የቻሉት፡ "እግዚአብሔር የለም" የሚሉ አሕዛብ በሠለጠኑባቸው ኅብረተሰቦች መካከል በመኾኑ ነው፤ ስለዚህ፡ "ኢትዮጵያዊ ነኝ!" በሚለው፡ ትውልድ ዘንድ፡ ውጤቱ፡ እንዲህ መኾኑ፡ ማንንም ሊያስደንቅ አይገባም፡፡

የሰዎች የኾኑት፡ እነዚህ ፍልስፍናዎች፡ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያውያን ዘንድ፡ ፈጽመው ሊሠሩና ሊጠቅሙ እንዳልቻሉ፥ ወደፊትም፡ በኢትዮጵያዊው፡ የሃይማኖት መሠረት ላይ ታንጸው ካልኾነ በቀር፡ ሊሠሩና ሊጠቅሙ  እንደማይችሉ፡ ካለፉት ተከታታይ ተሞክሮዎችና አኹን እየበረታ ከቀጠለው አሳዛኝ ኹኔታ፡ ይኸው ተረጋገጠ፡፡ ይህም የኾነው፡ የእግዚአብሔሩን በሚከተለው፡ በኢትዮጵያዊው ሥርዓትና በእነዚህ የሰዎች ፍልስፍናዎች መካከል ባለው፡ መሠረታዊ የባሕርይ ልዩነት ምክንያት መኾኑን፡ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ሊያውቀው ይገባል፤ በተለይም፡ በባዕዳኑ ትምህርት የተቀረፁትና የተራቀቁት፥ ያመኑትና የተማመኑት ምሁራን፡ ይህን እውነታ፡ ራሳቸው ተገንዝበውት፡ እየራሳቸውንና እነርሱ፡ "መሃይም" የሚሉትን፡ ወገናቸውን፡ ከዚህ ገዳይ ስሕተት ሊያድኑ ይገባቸዋል፡፡

በእነዚህ የሰዎች ፍልስፍናዎች ውስጥ ተጋንነው የሚወሱት፡ የግል ነጻነትን፥ የመብት መከበርንና የራስ አስተዳደርን የመሰሉት ዓላማዎች እኮ፡ ዛሬ፡ በምድር ላይ ካሉት የዓለም መንግሥታት ኹሉ፡ ቀዳሚ በኾነው፡ በኢትዮጵያዊው ሥርዓተ መንግሥት ዘንድ፡ ከፈጣሪ የታዘዙ መመሪያዎችና ዐበይት ተግባራት ኾነው፡ እየተሠራባቸው፥ እስከ፲፱፻፷፯ ዓ. ም. ድረስ፡ "ማኅበር" በሚለው አቋም፥ በተለይም፡ በአኵስም ጽዮን አስተዳደር፡ በአብነትና በሕያው ቅርስነት፡ በይፋ ሲካኼዱ ኖረዋል፡፡ የዛሬው ኢትዮጵያዊ ትውልድ፡ ይህን፡ የራሱን ሥርዓት፡ ከቁም ነገር ስላልቆጠረው፡ ንቆ እስከተወውና በትክክለኛው መንገድ እንዳይሠራበት፡ ኾነ ብሎ እስካገለለው ድረስ ማለት ነው፡፡

እንደዛሬው ኹሉ፡ በኢትዮጵያ ትውልዶች ላይ፡ በየዘመናቱ የሚደርሱት ሕዝባዊ መከራዎችና አገራዊ ውድቀቶች የሚከሠቱትና የሚደርሱት፡ ይህ እግዚአብሔራዊው የኢትዮጵያ ሥርዓተ መንግሥት ሲደፈርና ሲቃወስ መኾኑ፡ ተደጋግሞ ተነግሩዋልና፡ እዚህ ላይ፡ እንደገና ማተቱ አስፈላጊ አይኾንም።

እንግዴህ ወዲህማ፡ ኢትዮጵያዊው፡ ኹሉንም ዓይነት የሰዎች ፍልስፍና፡ ከነፈሊጦቹ ስላየው፥ በሙከራና በመከራም ስላለፈበት፡ ብዙ ጉድለትና ሓሰት ከተገኘበት፡ ከሰዎች የአገዛዝ ፍልስፍናና ፈሊጥ ይልቅ፡ በእግዚአብሔር ሥርዓተ መንግሥት እየተመሩና እየተዳደሩ መኖር፡ የተሻለና የበለጠ፡ መልካም ሕይወትን እንደሚያተርፍ፡ ራሱ አምኖ፡ ሌላውን እንደሚያሳምን አይጠረጠርም፤

ይህም፡ እውን የሚኾነው፡ እንኳንስ ለኢትዮጵያውያንና ለኢትዮጵያውያት፡ ለሌሎቹ የዓለም ሕዝቦችም ቢኾን፡ ሰዎች፡ እግዚአብሔርንና የእርሱ የኾነውን ኹሉ፡ በእውነት የሚፈልጉ፥ በእውነትም የሚሠሩበት ሲኾኑ ብቻ መኾኑ ሊታወቅ ይገባል።

## ሊበገር ያልተቻለው፡ የኢትዮጵያዊው/ዋ ኪዳናዊ ባሕርይ።

በዚህ አጭር ሓተታ እንደተብራራው፡ በጾመ ኢትዮጵያ አማካይነት፡ በተጸጸተ ልቦና፡ ወደእግዚአብሔር የሚቀርበው፡ የዚህ ኢትዮጵያዊ ትውልድ የንስሓ ጩኸት፡ አቀራረቡም፥ የሚያስከትለውም ውጤት፡ ከዚያ፡ ከሰውኛው የተለየ እንደሚኾን ግልጽ ነው። አዎን! ኢትዮጵያዊው አቤቱታ፡ በኢትዮጵያዊው ሥርዓት፡ ለእግዚአብሔር፡ በእውነትና በመንፈስ አምልኮ የሚቀርብ ስለኾነ፡ በጽሙናና በጸጥታ የሚፈጸም እንጂ፡ በጩኸትና በመፈክር፥ በሰልፍና በግርግር የሚካኼድ አይደለም።

ኢትዮጵያዊው ሥርዓት፡ "የእናት ምልጃ፡ ፊት አያስመልስ፤ አንገት አያስቀልስ!" እንዲሉ፡ እናት ኢትዮጵያ፡ ድንግል ማርያም፡ **<u>የሌላትና የቀረባት ምንም ነገር የለም እንጂ፡</u>** ቢኖራትም እንኳ፡ እጆቿን፡ ወደልጇ ወደእግዚአብሔር ዘርግታ፡ አቤቱታዋን፥ ፍላጎቷን፥ ጥያቄዋን፥ ወይም፡ ምስጋናዋን የምታቀርብበትና የምትገልጽበት ሃይማኖታዊ ምግባር ነው፤ ውጤቱ፡ በእምነት የሚጠበቅ፥ በሰዓታት ወይም በቀናት ሳይኾን፡ በቅጽበታት ውስጥ አስደሳች መልስን የሚያስሰጥ ኾኖ፡ ኹሉን-አቀፍ የኾነ፡ መልካም ፍሬን እንደሚያስገኝም አይጠረጠርም።

እማታውቁ ካላችሁ፡ እንድናሳውቃችሁ፥ "አውቀናል!" ብላችሁ፡ ነገር ግን፡ ለማመን ላልፈቀዳችሁ ደግሞ፡ በእግዚአብሔር እውነት፡ እናሳምናችሁ ዘንድ እንድትፈቅዱልን የምንጠይቃችሁ፡ አንድ ቍም ነገር አለ፤ እርሱም፡ "እውነተኛ" ኢትዮጵያዊን፡ በየዘመናቱ፡ ከሌላው ሰብአዊ ፍጡር ኹሉ የተለየ አድርገውት፡ በዓለሙ ኅብረተሰብ ዘንድ፡ የዛሬውን የመሰለ ችግርን ከፈጠሩበት ባሕርያቱ መካከል፡ ቀዳሚ ኾኖ የሚጠቀሰውን ይመለከታል፤ ***<u>ያም፡ ከማይገሠሠው ነጻነቱ ጋር፡ ከፈጣሪው በቀር፡ ሌላ ፍጡርን፥ ሌላ እውቀትን፥ ሌላ ሀብትን እና/ወይም፡ ሌላ ኃይልን፥ በገዢነት ለመቀበል፡ ፈቃደኛ አለመኾኑ ነው።</u>***

ለኢትዮጵያዊው፡ በሥጋውም፥ በነፍሱም፥ በመንፈሱም፡ ፈጣሪውና አምላኩ ብቻ ሳይኾን፡ አባቱና ሕይወቱ፥ ንጉሡና ካህኑም፡ "ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ" በተባለው፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ሰውነት የተገለጠው እግዚአብሔር ነው፤ እንዲሁም፡ እናቱና ሃይማኖቱ፥ አገሩና ንግሥቱም፡ "ኢትዮጵያ፡ ታበጽሕ እደዊሃ፡ ኀበ እግዚአብሔር!" የተባለችው፡ ቅድስት ድንግል ማርያም ናት፡፡ ከዚህ የተነሣ፡ ማንም ፍጡር፡ ቢወድም፡ ቢጠላም፥ ቢቀበለውም፡ ቢቃወመውም፡ ኢትዮጵያ፡ ጥንትም፥ ዛሬም፥ ለዘለዓለምም፡ ከነሕዝቧ፥ ከነመንግሥቷና ከነምድሩዋ፡ የእግዚአብሔር መኾኗን ማመን ግድ ይኾንበታል፡፡

ደግሞም፡ በአኹኑ ጊዜ፡ በአገር ውስጥም ኾነ በውጭ አገር፡ በእርሻ፥ በንግድ፥ በተግባረ እድ፥ በዘብና በውትድርና፥ በትምህርት፥ በጽሕፈት፥ በምሕንድስና፥ በኪነት፥ በሥነ ጥበብ፥ በድርሰት፥ በሕክምና፥ በዳኝነት፥ በአስተዳደር፥ በክህነትና በአማካሪነት፥ በሌሎችም ሙያዎች ላይ ተሠማርቶ፡ በገጠር፥ በሜዳ፥ በዱር በገደል፥ በብቸኝነት፥ በማይምነት፥ በረኃብ፥ በጥማት፥ በእርዛት፥ በደዌ ሥቃይ፥ በእሥራት፥ በስደት፥ በኀዘንና በድህነት የሚታገለው፡ ብቻ ሳይኾን፡ በከተማ፥ በመንደር፥ በቤት፥ በትዳር፥ በሥራ፥ በነጻነት፥ በጥጋብ፥ በምቾት፥ በጤንነት፥ በደስታ፥ በምሁርነትና በሥልጣን የተደላደለው ጭምር፡ "ኢትዮጵያዊ ነኝ!" ካለ፡ ራሱን፡ ለዚህ፡ ለኢትዮጵያዊው፡ የእግዚአብሔር ልጅነት፥ ለመንግሥቱም ዜጋነት፥ ወራሽነትና ካህንነት (አገልጋይነት)፡ ማብቃት ይኖርበታል፡፡

ታዲያ፡ "ዘለዓለማዊ ነጻነትን ካጎናጸፈኝ፡ ከእግዚአብሔር፡ በመልኩ በመፈጠሬ፥ ከመንፈሱም በመወለዴ፡ ፍጡሩና ልጁ፥ የመንግሥቱም ካህን=አገልጋይ፥ ዜጋና ወራሽ ኾኜ፡ በእርሱ ፈጣሪነትና አምላክነት፥ አባትነትና ንጉሥነት፥ በቅድስት እናቱም፡ በድንግል ማርያም፡ እናትነትና ሃይማኖትነት፥ አገርነትና ንግሥትነት ከመኖር በቀር፡ ለሌላ ባዕድ አልገዛም!" አስብሎ የሚያስጨክን፥ ይህን፡ የማይናወጽና የማይበገር ባሕርይን፡ ይኼ ኢትዮጵያዊ፥ ይኽችስ ኢትዮጵያዊት፡ ከቶ፡ ከየት አገኙት? ከፈጣሪያቸውና ከወላጆቻቸው፡ በተፈጥሮና በቃል ኪዳን ስለተቀበሉትና ስለወረሱት አይደለምን? አዎን! እውነታው፡ ይህ ነው፡፡

## ኢትዮጵያዊው ጾማችን፡ ጣፋጩን ፍሬ እንዲያስገኝልን።

እያንዳንዳችን፡ ኢትዮጵያዊነትን፡ እንዲህ፡ በነፍስ ወከፍ የተቀበልነውና የወረስነው፡- ፩ኛ፡ በቀጥታ፡ ከእግዚአብሔርና ከወላጆቻችን ከኾነ፥ ፪ኛ፡ ለእየራሳችን፡ በየግላችን፡ እንኖረውና እንጠቀምበት ዘንድ፥ እንገለገልበትና እናገለግልበትም ዘንድ ከኾነ፥ ፫ኛ፡ አኹንና ወደፊት፡ ሠርተንበት፥ የአገልግሎትና የንስሓ ፍሬንም አፍርተንበት የተገኘን ስለመኾኑ፡ እያንዳንዳችን፡ በየሕሊናችን፥ በወገናችንና በእግዚአብሔር ዘንድ፡ በነፍስ ወከፍ የምንጠየቅበት ከኾነ፡ ይህ፡ "ጾመ ኢትዮጵያ"፡ ለኹሉ የሚበጀውን ጣፋጭ ፍሬ ሊያበረክት ይበቃ ዘንድ፡ በትክክለኛው የእውነትና የመንፈስ ቅዱስ አምልኮ እንዲፈጸም የማድረጉ ኃላፊነት፡ የእየራሳችን መኾኑን ማወቅና ማረጋገጥ አለብን፡፡

ይህን ጾም፡ በእኛ እውነተኛነትና በመንፈስ ቅዱስ አምልኳችን ጸንተንና ተመርተን፡ እንዲህ ባለው፡ ሃይማኖታዊ ሥርዓት ኾነን ከፈጸምነው፡ እስካኹን ሲኾን እንደቆየው ኹሉ፡ አኹንም፡ እንደገና፡ ትንግርታዊ ውጤቱን ልናገኘው ይቻለናል፡፡ አዎን! የኃጢኣታቸው ጽዋ ሞልቶ፡ ሊጠፉ በቀረቡት፡ የሰዶምና የገሞራ ከተሞች ውስጥ፡ አሥር ጻድቃን ቢገኙ፡ ከተሞቹ እንደማይጠፉ፡ እግዚአብሔር፡ ለወዳጁ፡ ለአብርሃም አረጋግጦለት እንደነበረ ይታወሳል፤ አኹንም፡ ፈጣሪ፡ በዚህ ጾም ምክንያት፡ ምናልባት፡ እያንዳንዳችንን፡ "ከአሥሩ ጻድቃን መካከል፡ እንደአንዱ ቆጥሮ፡ የቃል ኪዳን አገሩን፡ ኢትዮጵያንና የቃል ኪዳን ሕዝቡን ኢትዮጵያውያንንና ኢትዮጵያውያትን፡ በበለጠ ይታደጋቸው፥ ከመጥፋትም ያድናቸው ይኾናል!" ብለን በማመን ብንጸመው፡ ይሠራልናል፡፡ (ዘፍጥ. ፲፰፥ ፳፪-፴፪፡፡)

እንግዲህ፡ በዚች፡ በሦስት ቀኖች "ጾመ ኢትዮጵያችን"፡ "ይህ ትውልድ፡ በሃይማኖት ተስፋ የሚጠብቀውን፡ ይህን የመሰለውን፡ መልካም ፍሬ ያስገኝለት ዘንድ፡ ምን ማድረግ አለበት?" ለሚለው ጥያቄ፡ መልሱን፡ እያንዳንዱ የትውልዱ አባል እንዲሰጥ ይጠበቅበታል፤ ይኸውም፡ "ራሴን፡ ከእግዚአብሔር ሕይወት ለይቼ ካጠፋሁበት አኗኗሬና ለሞት ከዳረግሁበት አስተሳሰቤ፡ አስቀድሜ፡ በእውነተኛ ንስሓ መልሼ ላዘጋጀው ይገባኛል!" የሚለው ነው፤ እንደነነዌ ሰዎች፥ ወይም፡ ከሕመሙ ለመዳን፡ በግድ፡ መራራ መድኃኒትን መውሰድና ከባድ ሕክምናን መቀበል እንዳለበት ጽኑ በሽተኛ ማለት ነው፡፡ አዎን! መሥዋዕትነትን፡ እንዲህ ለመክፈል፡ በቆራጥነት መዘጋጀትማ፡ ለእያንዳንዱ የትውልዱ አባል፡ አይቀሬ ግዳጅ መኾኑ መታወቅ ይኖርበታል፡፡ ትውልዱ፡ ከዚህ ግብ ለመድረስ፡ ይቻለው ዘንድ፡ የሚከተለውን፡ የቅዱሳት መጻሕፍት ቃል አስተውሎ ይፈጽመው ዘንድ፡ ይኸው ተጠቅሶለታል፡-

ይህም ቃል፡ ገናናውና ዘለዓለማዊው፡ ኢትዮጵያዊ መሪያችን፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ራሱን፡ እንደይቅር ባዩ ርኅሩኅ አባት፥ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ሃይማኖታቸው ጸንተው የሚገኙትን ወገኖች፡ እንደታላቁ ልጅ፥ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ሃይማኖቱን፡ በዓመፅ የካደውን፡ ይህን የዛሬውን የኢትዮጵያ ትውልድ ደግሞ፡ እንደአጥፊው ታናሹ ልጅ አስመስሎ፡ የዛሬ ኹለት ሺህ ሰባት ዓመት፡ በምሳሌ የነገረን ነው።

ስለዚህ፡ በንስሓ ለመመለስ "እምቢ!" ያለው፡ የዚህ ትውልድ አባል የኾነ ኹሉ፡ እየራሱን፡ በዚያ፡ በታናሹ አጥፊ ልጅ ቦታ በማስቀመጥ፡ መልእክቱን፡ በየግሉ ተቀብሎ፡ በአርአያነቱ ሊጠቀምበት ይገባል፡፡

**"አንድ ሰው፡ ኹለት ልጆች ነበሩት፤ ከእነርሱም፡ ታናሹ፡ አባቱን፡ 'አባቴ ሆይ! ከገንዘብህ፡ የሚደርሰኝን፡ ከፍለህ ስጠኝ!' አለው፡፡**

**"አባቱም፡ ከፍሎ ሰጠው፡፡**

**"ከጥቂት ቀን በኋላም፡ ያ፡ ትንሹ ልጁ፡ ገንዘቡን ኹሉ ሰብስቦ፡ ወደሩቅ አገር ኼደ፡፡ በዚያም፡ በመዳራት (በመሸታ ቤት በመደሰት)፡ ገንዘቡን ኹሉ አባክኖ፡ ጨረሰ!**

**"ገንዘቡን ኹሉ አባክኖ በጨረሰበት ጊዜም፡ በዚያ አገር፡ ጽኑ ረኃብ መጣ! እርሱም፡ ፈጽሞ ደኸየ፡፡ ኼዶም፡ ከዚያ አገር ሰዎች፡ ለአንዱ ተቀጠረ፡፡**

“ቀጣሪውም፡ አሳማዎችን ይጠብቅ ዘንድ፡ ወደእርሻው ቦታ ሰደደው፡፡ እዚያም፡ አሳማዎቹ በልተው ከሚተርፋቸው አሠር ለመመገብ እስከመፈለግ ድረስ ተራበ፤ ነገር ግን፡ ያንንም እንኳ፡ የሚሰጠው አላገኘም፡፡

“በዚህ ጊዜ፡ ወደልቡ ተመልሶ፡ እንዲህ ሲል አሰበ፡- "በአባቴ ቤት፡ እህል የሚተርፋቸው፡ አገልጋዮችና ደሞዝተኞች ስንቶች ናቸው? እኔ ግን፡ እዚህ፡ በረኃብ ልሞት ነው፡፡ ስለዚህ፡ አኹኑኑ ተነሥቼ፡ ወደአባቴ እኼዳለሁ፤ እንዲህም እለዋለሁ፡- 'አባቴ ሆይ! እኔ፡ በሰማይም፥ በፊትህም በድያለሁ፤ እንግዲህ ወዲህም፡ ልጅህ ልባል አይገባኝም፤ ከአገልጋዮችህ፡ እንደአንዱ አድርገኝ!'" ተነሥቶም፡ ወደአባቱ ኼደ፡፡

“አባቱም፡ ገና ከሩቅ ሲያየው፡ ራራለት፤ ሮጦ፥ አንገቱንም አቅፎ ሳመው፡፡

“ልጁም፡ "አባቴ ሆይ! በሰማይም፥ በፊትህም በደልሁ፤ ከእንግዲህ ወዲህም፡ ልጅህ ልባል አይገባኝም፤ ብቻ፡ ከአገልጋዮችህ፡ እንደአንዱ አድርገኝ፡፡" አለው፡፡

“አባቱም፡ አገልጋዮቹን፡ እንዲህ አላቸው፡- "ከኹሉ የተሻሉትን ልብሶች፡ ቶሎ አምጡና፡ አልብሱት! ለጣቱ፡ ቀለበት፥ ለእግሩም ጫማ አድርጉለት! የሰባ ፍሪዳም አውጡና እረዱ! እንብላ! ደስም ይበለን! ይህ ልጄ ሞቶ ነበር፥ ተነሥቷልና፤ ጠፍቶም ነበር፥ ተገኝቷልና፡፡" ደስም ይላቸው ነበር፡፡ (ሉቃ. ፲፫፥ ፲፩-፳፬፡፡)

አዎን! የዚህ ትውልድ የኢ-ሃይማኖታዊ ክፉ ግብር፡ አባሪ ተባባሪ የኾኑ ኢትዮጵያዊና ኢትዮጵያዊት ኹሉ፡ በዚህ ጾመ ኢትዮጵያችን አማካይነት፡ እንደዚህ፡ እንደታናሹ አጥፊ ልጅ፡ ከክህደትና ከዓመፅ፥ ከአመንዝራነትም ኃጢአታቸው፡ ከልብ ተጸጽተው፡ በእውነተኛ ንስሓ ሊመለሱ ይገባቸዋል፤ ይህን ካደረጉ፡ የፈጣሪያቸውን ይቅርታና ምሕረት፡ ያለጥርጥር እንደሚያገኙ፡ ይህ መለኮታዊ ቃል ያረጋግጥላቸዋል፡፡

የኢትዮጵያዊነታችን መገለጫና መታወቂያ ከኾኑት፡ ከሰባቱ ቅዱሳት ኪዳናት መካከል፡ በኢየሱስ ክርስቶስና በድንግል ማርያም የተቀዳጀነው፥ እኛም፡ በቅዱስ ቍርባን፡ ዘወትር የምናጸናው የቃል ኪዳን ማኅተም፡ <u>ኪዳነ ምሕረት</u> ነው፡፡ ይህንንም፡ በየዓመቱ፥ ዘንድሮም፡ ከዚች “ጾመ ኢትዮጵያ” በፊት ባለው፡ በወርኃ የካቲት፡ በ፲፮ኛው ቀን፡ በታላቅ የኢትዮጵያዊነት ስሜት በምናከብራት፡ የኪዳነ ምሕረት በዓላችን፡ እስከዛሬ፡ ለዓለሙ ኹሉ፡ በአዋጅ ስናሳውቅ ኖረናል፤ ዛሬም እናሳውቃለን፡፡

በመጨረሻ፡ የ“ጾመ ኢትዮጵያ” ምሕላችንን፡ ቸሩ አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስና ቅድስት እናታችን ድንግል ማርያም፡ ይቀበሉልን ዘንድ፥ ለምንጠብቀው መልካም የድል ፍሬም ልናበቃው ይቻለን ዘንድ፡ እያንዳንዳንችን፡ በእውነተኛው የኢትዮጵያዊነት የአምልኮ መንፈስ ኾነን፡ ልናቀርበው፥ ቅዱስ ቍርባንንም በመቀበል ልንፈጽመው እንደሚገባን፡ እስካኹን ከተሰጠው ማብራሪያ፡ በሚበቃ የተገነዘባችሁት ይመስለናል፡፡

እንዲህ ከኾነ፡ ኢትዮጵያዊ ማንነታችንንና የኢትዮጵያዊነታችንን ምንነት፡ አስቀድመን፡ ለየራሳችን፡ በትክክልና በግልጽ ማወቅ፥ ቀጥለን፡ ይህንኑ ማንነታችንንና ምንነታችንን፡ ለእግዚአብሔርና ለሌላው ሰብአዊ ፍጡር፡ ማሳወቅ አለብን።

ይልቁንም፡ ያለንበት ዘመን፡ እጅግ አሳሳችና አደናጋሪ በመኾኑ፡ የዚህኑ፡ የኢትዮጵያዊነታችንን፡ እውነተኛነቱን ብቻ ሳይኾን፡ ከማናቸውም ዓይነት ሰብአዊ ስሕተትና ሰይጣናዊ ሓሰት ሳይቀር፡ የጠዳና የጠራ፥ ፍጹም መለኮታዊና ንጹሕ ኢትዮጵያዊ መኾኑንም፡ ማረጋገጥ ግድ ይኾንብናል፡፡ ይህን የመሰለውን ጥንቃቄ እናደርግ ዘንድ፡ ያለፍንበትና የምንገኝበት መከራ፡ አስተምሮናል፡፡

ስለዚህ፡ በዚህ ረገድ ያለውን ፍላጎታችንን ሊያሟሉልን የሚችሉ፡ አራት የኢትዮጵያዊነት መመሪያ ክታቦች፡ ግእዙ ብቻ ሳይኾን፥ ኢትዮጵያኛውና እንግሊዝኛው ቅጂዎች ጭምር፡ ከዚህ መልእክት ጋር ተያይዞ፡ ከነዜማው በቀረበው፡ የጾመ ኢትዮጵያ ሥርዓተ ጸሎት ውስጥ ታገኟቸዋላችሁ፤ እነዚህ ጽሑፎች፡ የኢትዮጵያዊነትን መሥፈርቶች ያካተቱና በጸሎት መልክ የተዘጋጁ፥ እግዚአብሔር፡ እንደተስፋ ቃሉ፡ በእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ፥ በእያንዳንዷም ኢትዮጵያዊት ልብ ላይ የጻፋቸውንና በየልቦናው ውስጥ ያሳደራቸውን ቅዱሳት ኪዳናት የያዙ ናቸውና፡ በማስተዋልና በማተኰር ተጠቀሙባቸው፡፡

ደግሞም፡ በዚህ መልእክት ውስጥ ስለተጠቀሱት ቁም ነገሮች፡ በበለጠ ለማወቅና በዝርዝር ለመረዳት፡ ከዚህ የሚከተሉትን መጻሕፍት፡ በኢትዮጵያና በውጭ አህጉራት አብያተ መጻሕፍትና መደብሮች፥ ወይም፡ በዚህ፡ በአገልግሎታችን የጎዋ ሰሌዳችን ላይ በተጻፉት አድራሻዎች በኩል፡ ልታገኟቸውና ልትመለከቷቸው ይቻላል፡፡ እነዚህም፡- **"ኢትዮጵያዊው፡ በማንነቱ ፍለጋ!"፥ "ኢትዮጵያ፡ የዓለሙ መፋረጃ!" Ethiopia: The Classic Case** እና **"ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት"፡- "አንደኛ መጽሓፍ"፥ "ኹለተኛ መጽሓፍ"፥ "ሦስተኛ መጽሓፍ"፥ "ምሥራች፡ ከእናት ኢትዮጵያ! ለኢትዮጵያ ልጆች፤ ስለኢትዮጵያዊነት፥ "ለኢትዮጵያ ሕፃናት፡ የቅዱሱ ኪዳን ሥርዓተ ትምህርት!" እንዲሁም፡ "አዳም እና ሔዋን፡ በኢትዮጵያ!"** የተባሉት ናቸው፡፡

እነዚህ መጻሕፍት፡ ለበርካታዎቹ የዘመኑ ጥያቄዎች፡ የሰውኛውን የ"እውነት" አቀራረብ ፈሊጥ በመከተል ሳይኾን፡ የእግዚአብሔር በኾነችው፡ መለኮታዊት እውነት ላይ በተመሠረተ፡ ቀጥተኛነትና ግልጽነት፡ ትክክለኞችን መልሶች የሚሰጡ ናቸው፡፡ ከጥያቄዎቹም መካከል፡ እንዲህ የሚሉ ጥቂቶቹ ይገኛሉ፡-

**"ኢትዮጵያ ማን ናት? ኢትዮጵያዊው ማን ነው? ኢትዮጵያዊነትስ ምንድር ነው? እኔ ማን ነኝ? እግዚአብሔር ማን ነው? ባልንጀራዬስ ማን ነው? የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያን ኹኔታ፡ እስከ፲፱፻፷፯ ዓ. ም. ድረስ፡ እንዴት ነበር? ከዚያ በኋላና እስካኹን ያለውስ እንዴት ነው?**

**"በ፲፱፻፷፯ ዓ. ም. የደረሰውን ታላቅ ውድቀትና ጥፋት ያመጣው ጠንቅ፡ በእርግጥ ምንድር ነው? ከኹሉም በላይ፡ ለዛሬውና ለወደፊቱ፥ ለጠቅላላውም የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያን ችግር፡ ፍጹሙና ዘለዓለማዊው መፍትሔ፡ ከቶ ምንድር ነው?"**

ይህ መልእክት፡ በማናቸውም ዓይነት መስመርና መልኩ የሚደርሳችሁ ኹሉ፡ እያንዳንዳችሁ፡ በኢትዮጵያዊነታችሁ፡ ራሳችሁ ተቀብላችሁ፡ እንድትፈጽሙት ብቻ ሳይኾን፡ ዓቅማችሁ በፈቀደ መጠን፡ ለሌሎችም እንድታስተላልፉት ያስፈልጋል። ለዚህም፡ በሥጋና በነፍስ፥ በመንፈስም፡ ኃላፊነትና አደራ፥ ተጠያቂነትም እንዳለባችሁ፡ ልታውቁት ይገባል፤ ይህን ኃላፊነት፥ አደራና ተጠያቂነት የተቀበላችሁትም፡ ከሰው ሳይኾን፡ ከመክሊቶቹ ባለቤቶች፡ ከአምላካችን፡ ኢየሱስ ክርስቶስና ከእናታችን ድንግል ማርያም ስለኾነ፡ በፊታቸው በምትቀርቡበት ጊዜ፡ ከፍሬው፥ ወይም፡ ከትርፉ ጋር እንድታስረክቧቸው የሚጠይቋችሁ፡ እነርሱ መኾናቸውን፡ የተገነዘባችሁት ይመስለናል።

የ“ጾመ ኢትዮጵያ” ማሳሰቢያ የኾነው፡ ይህ መልእክት ደርሷችሁ፡ ጾሙን፡ ለመፈጸም ፈቃደኞች ከኾናችሁ፡ እያንዳንዳችሁ፡-

፩ኛ፡ የመንፈስ ቅዱስ ወገን መኾናችሁን፡ በይፋ መመስከራችሁ ነው፤ ይህም፡ በኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል ምልክት እያማተባችሁ፡ “በስመ እግዚአብሔር አብ፥ ወወልድ፥ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ፥ በቅድስት ሥላሴ፡ እንዘ አአምን፥ ወእትመነሶን፤ እክሕደከ ሰይጣን! በቅድመ ዛቲ፡ እምየ ቅድስት ኢትዮጵያ፡ መንግሥተ እግዚአብሔር፡ እንተ ይእቲ፡ ስምዕየ ማርያም ጽዮን፤ ለዓለም ዓለም።”

ማለትም፡ “አንድ አምላክ በኾነው፡ በእግዚአብሔር አብ፥ ወወልድ፥ ወመንፈስ ቅዱስ ስም አምኜና ተማጽኜ፡ እግዚአብሔር እምና የእኒህ ሦስትነት መንበረ ጸባኦት፥ እናቴና መጠጊያዬ፥ ምስክሬና የእግዚአብሔር መንግሥት ኢትዮጵያ በኾነችው፡ በቅድስት ድንግል ማርያም ፊት፡ አንተን ሰይጣንን ክጄሃለሁ! ለዘለዓለሙ።” ብላችሁ በምትጀምሩት ጸሎታችሁ ይታወቃል፤

፪ኛ፡ እውነተኛ ኢትዮጵያዊነታችሁን፡ በገሃድ ማረጋገጣችሁ ነው፤ ይኸውም፡ በዚህ ድርጊታችሁ፡ ፈጣሪያችሁን፡ ከነእናቱ፡ ማስደሰታችሁ፥ የየግላችሁን ኢትዮጵያዊ ግዳጅም፡ መወጣታችሁ ነውና፡ በጾሙ ማብቂያ ጊዜ፡ በመንፈስ ቅዱስ ተመልታችሁና ረክታችሁ፡ እየራሳችሁን ደስ ብሏችሁ ታገኙታላችሁ።

መሓሪው ፈጣሪያችን፡ የ“ጾመ ኢትዮጵያ” ምግባራችንን በሰላም አስፈጽሞ፡ የቃል ኪዳናችን ፍሬ የኾነውን፡ ምሕረቱን፡ ለዘወትር ለመቀበል የተዘጋጀን ኾነን እንገኝ ዘንድ እንደሚያበቃን እናምነዋለን!

\+ + + + + + +